CITE AS: Cochrane, L. and Thornton, A. (2017) A Socio-Cultural Analysis of Smallholder Borrowing and Debt in Southern Ethiopia. Journal of Rural Studies 49:69-77.

# በደቡብ ኢትዮጵያ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ተበዳሪ ገበሬዎች እና የዕዳ ሁኔታ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ትንተና

ሎጋን ኮክሬን፣ አሌክ ቶርንቶን

ዩኒቨርስቲ ኦቭ ብሪቲሽ ኮሎምቢያ፣ አካናጋን፣ ካናዳ

ዘ ዩኒቨርስቲ ኦቭ ኒው ሳውዝ ዌልስ፣ ዩ.ኤን.ኤስ.ደብሊው ካንቤራ፣ ካንቤራ፣ 2612 አውስትራሊያ

**አጠቃልሎ**

ይህ ጥናት ሁለቱንም ኳሊታቲቭ እና ኳንቲታቲቭ የምርምር ዘዴዎችን በመጠቀም በደቡብ ኢትዮጵያ በመበደር እና ዕዳ ሂደት ውስጥ ያለውን የገጠር የፋይናንስ ስርዓት እና ድግግሞሽ ውስብስብነት አነስተኛ የመሬት ይዞታ ባላቸው ገበሬዎች መካከል የተደረገ የዳሰሳ ጥናት ነው፡፡ በአንድ ግብረ አካባቢያዊ ጥናት መቼት ውስጥ አካባቢያዊ መገኛን ለመሠረተ-ልማት፣ ገበያ እና አገልግሎቶች ካለ ቅርበት ጋር በማነጻጸር እነዚህ ግብዓቶች የተበዳሪነት ድግግሞሽ፣ ምንጭ፣ መጠን እና የሚወሰነውን የወለድ መጠን፣ የመልሶ ክፍያ ቀነ ገደብ እና የተበዳሪነት እንዲሁም የዕዳ መጠን ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ እንፈትሻለን፡፡ ጥናት በተካሄደባቸው ማኅበረሰቦች መካከል ፣ የተበዳሪነት አካባቢያዊ ሁኔታ እና የዕዳን  እንዲሁም አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች የተበዳሪነት እና እዳ ዑደቱን አሸንፈው ንብረት እንዲያበጁ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞችን መቅረጽ ወይም ማስተካከልን ለማገዝ የሚያስችሉ ገደቦችን እና ዕድሎችን ጠቀሜታ የሚያመላክት ልዩነት አግኝተናል፡፡

## 1. መግቢያ

በገጠራማው የአፍሪካ ክፍል ውስጥ፣ በተለይም አነስተኛ የመሬት ይዞታ ባላቸው ገበሬዎች መካከል ከአጭር ጊዜ ያለፈ የገንዘብ ቁጠባ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ተግባራዊ አይደረግም (Cullet al., 2013)፡፡  በገጠር በሚኖሩ ማኅበረሰቦች መካከል ይህ የሚሆነው፣ መደበኛ የባንክ አገልግሎት አቅርቦት እና መገኘት ውስን ከመሆኑ የተነሳ ለቁጠባ እና ድንገተኛ ክስተቶችን ለመቋቋም የሚያችል ዕድል የመፍጠርን ሁኔታ ይቀንስዋል (Salami et al., 2010)፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በገጠራማው የኢትዮጵያ ክፍል የሚኖሩ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች የሚቆጥቡት ገንዘብ አይኖርም ወይም ጥቂት ይሆናል፣ እንዲሁም የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማግኘት ያላቸው ዕድል እጅግ አንስተኛ ነው (Amha, 2011)፡፡ እንደ መንግሥት (GoE, 2010)፣ ዓለም-አቀፍ አካላት (World Bank, 2013)፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት (Chiche and Kelemu, 2012; Chemonics International, 2006) እና ተመራማሪዎች (Gecho, 2014; Handino, 2014; Tesfamariam, 2012) ከሆነ፣ የገንዘብ ቁጠባ ያለመኖሩ ደካማ የሆነው የቁጠባ ባህል ያስከተለው ስለ ሆነ መርሀግብሮች የሚያተኩሩት በባህሪ ለውጥ ተግባቦት እና ትምህርት ላይ ነው፡፡ ይህ ጥናት ገቢን ከመቆጠብ ወይም ንብረትን ከማፍራት የሚያግደው አብይ ምክንያት ውዝፍ ዕዳ መሆኑን በማሳየት በገጠራማው ክፍል ስለሚታየው የዕዳ ሁኔታ  የተደረጉ ጥናቶችን ውጤት ያጠናክራል ፡፡ ለምሳሌ በKrishna (2010) ጥናት እንደ ታየው፣ ጥናት ባካሄደባቸው አምስት ሀገራት ውስጥ ቤተሰቦች ድሀ ለመሆናቸው ዋነኛው ምክንያት ዕዳ ሊሆን ይችላል፣ እንዲሁም Scott (1985) እንዳሳየው ዕዳ መሬትን ከማጣት የተነሳ ሊከሰት የሚችል ሲሆን፣ (ከፊል -) ቋሚ የባለ ዕዳነት ሁኔታን በማስከተል እነዚያ ቤተሰቦች ዕድሜ ልካቸውን ዕዳ ከፋይ ሆነው እንዲቀሩ የሚያደርግ ነው፡፡ በዕዳ፣ ቁጠባ እና ብድር ላይ የተካሄዱ አንዳንድ ትንታኔዎች  በግለሰቦች፣ ቤተሰቦች እና ማኅበረሰቦች ላይ የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ በመግለጥ የተሻለ ዕይታ እንዲኖር አስችለዋል (Case et al., 2013; Gray and Dowd-Uribe, 2013; Guerinet al., 2013; Mohanty, 2005)፡፡ ነገር ግን፣ ዕዳ በመንግስታት፣ በልማት ተቋማት እና በተመራማሪዎች ዘንድ፣ በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ የተሰጠው ትኩረት እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ይህ የዳሰሳ ጥናት አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች ከብድር እና ዕዳ ጋር ያላቸውን ቁርኝት በስፋት ለመረዳት አስተዋጾ የሚያደርግ ሲሆን፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች የዕዳ ሁኔታ በጥቂቱ ያሳያል፡፡

በሚከተሉት ክፍሎች እነዚህን ጉዳዮች ከማህበራዊ-ባህላዊ እይታ አንጻር ከሚዳስስ ጠቃሚ ጽሑፍ በመነሳት አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎችን የባለዕዳነት አውድ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ እና ሦስተኛው ክፍች ደግሞ ጥናቱ የተካሄደበትን ስፍራ ዳራ እና የተጠቀምነውን የጥናት ዘይቤ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ አራተኛው ክፍል በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙት አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች ላይ የተካሄደው ጥናት ያስገኛቸውን ምልከታዎች ያሳያል፡፡ ይህ መረጃ የኢትዮጵያ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች ያለባቸውን የባለ ዕነት መጠን፣ ዓይነት እና ድግግሞሽ በተመለከተ አዲስ መረጃን የያዘ ነው፡፡ ስመ ጥሩ የሕብረተሰብ ጥናት እና የግብርና መሻሻል ባለሙያ የሆነው ኢትዮጵያዊው ደሳለኝ ራህማቶ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች የዕዳ ሁኔታ እስከነ አካቴው ትኩረት እንዳልተሰጠው አስተያየቱን አስፍሯል (Rahmato, personal communication, 25 June 2015)፡፡ እስከ አሁኑ ጊዜ ድረስ፣ ባለዕዳነት የሚያስከትላቸውን ችግሮች በምሳሌነት የሚያጣቅሱ ሪፖርቶች እና ከአበዳሪ ትስስሮች ምልከታ አንጻር መደበኛ ያልሆነ የብድር አገልግሎት እና ቁጠባን የሚያሳዩ ጥናቶች ብቻ ናቸው በጉዳዩ ላይ ሊገኙ የሚችሉት (Aredo, 1993; Caudell et al., 2015)፡፡ ይህ ጥናት የገጠርን የፋይናንስ ስርዓት ውስብስብነት እና የተበዳሪነት እና የዕዳ ድግግሞሽ ዐብይ ግብ አድርጎ ይተነትናል፡፡ ከዚህ በፊት በተሠሩ ጥናቶች ላይ ያካሄድነው ቅኝት እንደሚያመላክተው እንዲህ ያሉ ጥናቶች በተለይም ከዕዳ ስፋት፣ ምክንያት እና ምንጭ ጋር፤ እንዲሁም ከወለድ መጠን እና ከብድር ድግግሞሽ ጋር በተያያዘ የሚካሄዱ ጥናቶች በኢትዮጵያ ዐውድ ውስጥ የሚሰጣቸው ከተገቢው ስፍራ ያነሰ ነው፡፡ በዚህ ጥናት እነዚህን በግልጽ የሚታዩ ክፍተቶች ለመሙላት መንደርደሪያ የሚሆኑ አዳዲ እይታዎችን ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ እንዲያም ቢሆን፣ ጥናቱ ሁሉንም የገጠር የፋይናንስ ስርዓትን ውስብስብ ገጽታዎች፣ የብድር ድግግሞሽ እና ዕዳ በገጠር አነስተኛ የመሬት ይዞታ ባላቸው ገበሬዎች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለማሳየት የታቀደ አይደለም፡፡ ይልቁኑም የብድር መጠን፣ ድግግሞሽ እና ምንጮችን በተመለከተ የተደረገን ግምገማ ያሳያል፡፡ ይህ ጥናት በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ ጥናቶች እንዲካሄዱ መሠረት እንደሚሆን እና እንደሚያበረታታ ተስፋ እናደርጋለን፡፡

## 2. ዐውድ

እንደ አነስተኛ የብድር እና ቁጠባ ተቋማት ያሉ ዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ያላቸውን ለመደገፍ የታሰቡ አካሄዶች ሌሎች ጥናቶች በተመሳከሩበት ክፍል ውስጥ ግለሰቦች እና ቤተሰቦች ድህነትን ለማስወገድ የሚችሉባቸው መንገዶች ተደርገው በሰፊው ይታሰባሉ፡፡ ነገር ግን፣ የብድር ዕና የዕዳን ሚና በተመለከተ የተሰጠው ትኩረት የተወሰነ ነው፡፡ በቀጣይነትም ትኩረት ተሰጥቶ ጥናት የሚደረገው በቢሊዮን በሚቆጠሩ ዶላሮች የሚገመተውን ምላሽ ያላገኘ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች የብድር ጥያቄ ላይ ነው (ISF, 2013)፡፡ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች የፋይናንስ ስርዓቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚቀሰቅሱ ሪፖርቶች ውስጥ ገበሬዎች ገንዘብ እየተበደሩ እንደ ሆነ እና የወለድ መጠንም እጅግ ከፍተኛ ሊሆን ከመቻሉ የተነሳ የረዥም ጊዜ ዕዳን ሊያስከትል እንደሚችል እውቅና ተሰጥቷል፡፡ ሆኖም የስፋቱን ሁኔታ በተመለከተ ያለው ግዝቤ አነስተኛ ነው፡፡ የምርምር ውጤቶች በሚለካው ጉዳይ፣ በልኬቱ በሚሳተፉት ሰዎች፣ ጥናቱ በሚካሄድበት ስፍራ እና መረጃው በሚሰበሰብበት ዓመት የሚወሰን ይሆናል (Chambers, 1995)፡፡ መለኪያዎችን ከመምረጥ እና አንዳንድ መለኪያዎችንም ፈጽሞ ከማስቀረት የተነሳ አሉታዊ ወይም ያልተጠበቀ ውጤት ሊገኝ ይችላል (Cochrane and Thornton, 2016)፡፡ በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች፣ ፖሊሲ አውጪዎች የዕዳን ተጽዕኖ ከድህነት ቅነሳ አካል አንዱ አድርገው የማይቆጥሩ ሲሆን፣ በምዘና እና የቤት ለቤት የዳሰሳ ጥናት ወቅትም የሚካተተው አልፎ አልፎ ነው፡፡

ዊልሰን (2009: 84) "ገበሬዎችን ለመደገፍ የሚወጡ ፖሊሲዎች እና መርሀ-ግብሮችን ከረዥም ጊዜ ባለ ዕዳነት ዐውድ አንጻር ልንረዳ ያስፈልጋል" ሲል ይሟገታል፡፡ ነገር ግን፣ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች የብድር እና የባለ ዕዳነት ሁኔታ የሚመለከት በቂ መረጃ በተለይም በኢትዮጵያ ዐውድ አይገኝም፡፡ አነስተኛ ይዞታ ባላቸው ገበሬዎች የዕዳ ሁኔታ ላይ በሌሎች ሀገራት የተካሄዱ ጥናቶች በጉዳዩ ላይ ጥቂት ብርሀን ይፈነጥቃሉ፡፡ እንደ ሕንድ (Krishna, 2010)፣ ሳሞአ (Thornton et al., 2010) እና ደቡብ አፍሪካ (Case et al., 2013) ያሉ ብዝሀነት ያላቸው መቼቶች ውስጥ እንደታየው ማኅበራዊ ግዴታዎች በዕዳ ላይ አስተዋጾ ያደርጋሉ፡፡ በደቡብ አፍሪካ በተደረገው ጥናት እንደ ታየው፣ የቀብር ስነ ስርዓቶች ማህበራዊና ህህላዊ እሳቤዎች በተያያዙበት እና ውድ ወጪ በሚያስወጣ ሁኔታ የሚካሄዱ ሲሆን፣ ከእነዚሁ ውስጥ አንድ አራተኛ የሚያህሉት የተከናወኑት በብድር በተገኘ ገንዘብ ነው (Case et al., 2013)፡፡ እንዲህ ያሉ ማኅበራዊ ግዴታዎችን ለማካሄድ አለመቻል ለረዥም ጊዜ የሚዘልቅ አሉታዊ ማኅበራዊ ሁኔታ ላይ ይጥላል፡፡ ሌሎች ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ደግሞ፣ ብድር ለሌሎች እንደ ሠርግ (በሕንድ) ላሉ ማኅበራዊ አቋምን ሊያጠናክሩ ለሚችሉ ስነ ስርዓቶች ይውላል (Bloch et al., 2004)፡፡ ይህኛው ጥናት Case et al. (2013) ዕዳ እና ባህላዊ-ማኅበራዊ ስነ ስርዓቶች ያላቸውን ቁርኝት በተመለከተ ጥሩ መረጃን የሚያስጨብጥ ቢሆንም፣ ሌሎች ማኅበረሰቦ ደግሞ ባለ ዕዳነትን የሚያስወግዱ እንደ ከንረቤቶች እና እንግዶች የሚገኙ ስጦታዎች የመሳሰሉ ማኅበራዊ-ባህላዊ ልምምዶች አሏቸው (Ainsworth and Over, 1997; Stover and Bollinger, 1999)፡፡ እነዚህ መጠነ-ሰፊ የአንድ ጊዜ ነገር ግን እጅግ ብዙ ወጪ የሚያስወጡ ማኅበራዊ ስነ ስርዓቶች በጥናት እና ምርምር ዓለም ውስጥ ትኩረትን የሳበ ቢሆንም፣ ገበሬዎች እና ቤተሰቦቻቸውን በዕዳ እንዲዘፈቁ የሚያደርጉ የዕለት ተዕለት ወጪዎች ላይ እምብዛምም ጥናት አልተካሄደም፡፡ የዕዳ እና ባለዕዳነት ክብደት በቀላሉ ሊታይ አይገባም፡፡ ምክንያቱም መሬትን እና የገቢ ምንጭን ማጣትን ከማስከተሉም አልፎ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች ነፍሳቸውን እንዲያጠፉ ምክንያት ሆኗል (Mohanty, 2005)፡፡

Gray and Dowd-Uribe (2013) እንዲሁም Thornton et al. (2010) ዕዳን ወደ ብድር ፍላጎት ከሚገፋፉ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ጋር በማያያዝ በማኅበረሰብ አባላት መካከል ልዩነት የሚያመጣ ጉዳይ መሆኑን ያወሳሉ፡፡ ሁለቱም ጥናቶች በቤተሰቦች መካከል ልዩ ልዩ የተበዳሪነት ሁኔታዎች የሚገኙበትን መጠን በማሳየት ለሁኔታዎቹ አስተዋጾ የሚያደርገውን ሂደት ከዐውዱ አንጻር ያሳያሉ፡፡ በቡርኪና ፋሶ የግብርና ዐውድ ውስጥ ከፍተኛ ዕዳ ያለባቸው እና በተደጋጋሚ የሚበደሩት ድሆች ሲሆኑ፣ በአንጻራዊነት የተሻለ የገንዘብ አቅም ላይ ያሉት ደግሞ ባላቸው ማኅበራዊ ተቀባይነት፣ አባል የሆኑባቸው ማኅበራት ውስጥ ከሚገኙ ባለጸጋ አባላት በሚያገኙት ድጋፍ አማካኝነት እዳ ውስጥ ከመዘፈቅ ይተርፋሉ (Gray and Dowd-Uribe, 2013)፡፡ በአንጻሩ፣ ብዙ መሬት እና አቅርቦቶች ያሏቸው የታይላንድ ገበሬዎች ደግሞ፣ መሬታቸው ላይ የግብርና ሥራን ለማከናወን ትልቅ ካፒታል የሚያስፈልጋቸው ከመሆኑ የተነሳ እና አበዳሪዎችም ብድርን ይከፍላሉ ብለው ስለሚያምኑባቸው ባለ ብዙ ዕዳ ይሆናሉ (Nuansoi,

2013)፡፡ በላቲን አሜሪካ ያለው የዕዳ ሁኔታ ላይ የተካሄደ ጥናት ደግሞ ገበሬዎች የረዥም ጊዜ ዕዳን ለመቅረፍ እንደሚጣጣሩ ሲያሳይ፣ ትክክለኛ መንስዔዎቹ አከራካሪ ሲሆኑ ስልታዊ ምርምር አልተካሄደባቸውም (Bacon et al., 2014; Wilson, 2010)፡፡ እነዚህ ልዩ ልዩ ምሳሌዎች የሚያሳዩት የገጠሩ የፋይናንስ ስርዓት ውስብስብ እና በጎጥ የተወሰነ እንደ ሆነ ነው፡፡

በገጠራማው የደቡብ ሕንድ ክፍል የተካሄደ ጥልቅ ጥናት ብድርን በማግኘት ቀረቤታ፣ ዋጋ እና አጠቃቀም ላይ መገኛ ያለውን ጠቃሚ ሚና እና የሕብረተሰብ ጎራ፣ መደብ እና መገኛ ያላቸውን አስተዋጾ ነጥሎ አሳይቷል (Guerin et al., 2013)፡፡ የጥናቱ ባለቤቶች ዕዳ የገንዘብ ጉዳይ ብቻ ተደርጎ መታየት እንደ ሌለበት፣ ይልቁንም ባለው ማህበራዊ-ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና መልከዓ ምድራዊ መቼት ውስጥ እንደሚከናወን ቀዳሚ ማኅበራዊ ግብይት ተደርጎ ቢታሰብ እንደሚሻል ያትታሉ፡፡ (Guerin et al., 2013) እንደሚያመላክቱት፣ የማኅበራዊ ግንኙነት አካባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታዎች እና ሂደትን የሚቀርጹ የዕዳ ሁኔታዎችን በተመለከተ ግንዛቤ በሚኖርበት ሁኔታ ብቻ ነው ፖሊሲዎች ተገቢ፣ ጠቃሚና ግባቸውን ለመምታት የሚችሉ የሚሆኑት፡፡ በልሂቅ ደረጃ ሲታይ (Fridell, 2013: 1492; Soederberg, 2013) የዕዳ አካሄድ የሚበጀው "እኩል ባልሆኑና ፉክክር በሞላባቸው መዋቅሮች እና ግንኙነቶች" እንደ ሆነ ሁሉ፣ እነዚህ ሂደቶች በደቂቅ ደረጃ በገጠር የግብርና መቼት ውስጥ የሚታዩ ቢሆንም፣ ስለሁኔታው እምብዛምም ዕውቀት የለም፡፡

Gray and Dowd-Uribe (2013) እና (Guerin et al., 2013) ካደረጓቸው ጠቃሚ አስተዋጾዎች በተጨማሪ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው በግብርና የሚተዳደሩ ማህበረሰቦች የዕዳ ይዘት፣ መጠን እና ድግግሞሽን፣ የብድር ምክንያትን፣ የብድር ምንጮችን እና እንዲከፍሉ የሚጠበቅባቸውን የወለድ መጠን ማዕከል በማድረግ ሌሎች ጥቂት ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ሆኖም፣ ዕዳ ሲታከልበት የፖሊሲዎች እና መርኃ-ግብሮች ተገቢ ያለ መሆን በግልጽ ይታያል (Guerin et al., 2013)፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ ከቁጠባ እና ንብረት ማፍራት የሚያግዱት ማነቆዎች ውጤታማ እና ግብ የሚመቱ ፖሊሲዎ እና መርሀ ግብሮችን ለመቅረጽ ብዘሀነት እና ዝርዝር ጉዳዮችን በጥልቀት ማወቅ ማስፈለጉን ያመላክታል (Gray and Dowd-Uribe, 2013)፡፡ ይህ ጥናት በተጨማሪም አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸውን ገበሬዎች የዕዳ ሁኔታ ዝርዝር ማካተትን ጠቃሚነት ጨምሮ የዕዳ ሁኔታ በገጠሪቱ ደቡብ ኢትዮጵያ ያለበትን የተለየ ሁኔታ ምልከታዎች ያሳያል፡፡ የጥናቱ ግኝት በኢትዮጵያ፣ በተለይም በመንግሥት የሚተዳደሩ አነስተኛ የብድር ተቋማት መጠን እየጨመረ በሚገኝበት ሁኔታ የተሻለ ግንዛቤ የታከለበት የፖሊሲ ውይይት እንዲካሄድ ሊያበረታታ ይችላል፡፡ የዳሰሳ ጥናት እንደ መሆኑ፣ ይህ ጥናት በፖሊሲ እና መርሀ ግብር ላይ ማሻሻያ ሊደረግባቸው የሚገቡ አቅጣጫዎችን ለመጠቆም የታለመ ሳይሆን ፖሊሲ አውጪዎች እና መርሀ ግብር የሚቀርጹ አካላት የሚሰቱት አገልግሎት ተገቢ እና ውጤታማ መሆን ያለመሆኑን የሚያነጻጽሩበት እና ተጨማሪ ጥናቶች እንዲካሄዱ የሚያስችል መሠረታዊ ግርፍ መረጃ የሚገኝበት ነው፡፡

### 3. ጥናቱ የተካሄደበት ስፍራ

ኢትዮጵያ ግብርና መራሽ ምጣኔ ሀብት ያላት ሲሆን፣ ከ80% የሚበልጠው ሕዝቧ የሚኖረው በገጠራማው የሀገሪቱ ክፍል ነው(CIA, 2015)፡፡ ሀገሪቱ በክልላዊ መንግስታት እና አስተዳደራዊ ከተማዎች የተዋቀረች ስትሆን ከአጠቃላይ ሕዝቡ አራት-አምስተኛ የሚሆነውን ብዛት የሚይዙት የኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች (ደ.ብ.ብ.ሕ) ሕዝባዊ ክልላዊ መንግስታት ናቸው (CSA, 2007)፡፡ የደ.ብ.ብ.ሕ ክልል ከፍተኛ የሆነ የገጠር ነዋሪ ሕዝብ ብዛት ያለው መሆኑ ከሌሎቹ ክልላት ለየት ያደርገዋል፡፡የደ.ብ.ብ.ሕ አስራ ሁለቱም የገጠር ቀጠናዎች በጠቅላላ የሕዝብ እፍጋት መጠናቸው በስኩዌር ኪሎ ሜትር ከ500 ሰው በላይ ነው (CSA, 2007)፡፡ በአንጻራዊነት ዝናብ ከሚያገኙት ደጋማ ስፍራዎች እና ዝናብ ከተመናመነባቸው የምስራቅ ደጋማ ስፍራዎች በተለየ መልኩ፣ ማዕከላዊው የደ.ብ.ብ.ሕ ክልል የማያስተማምን የዝናብ መጠን የሚያገኝ መሆኑ ሙሉ በሙሉ በዝናብ ላይ በተመሠረተ እርሻ የሚተዳደሩ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች ላይ ፈታኝ ሁኔታን ይፈጥራል (Cochrane and Gecho, 2016; CSA, 2007)፡፡

ይህ ጥናት በደ.ብ.ብ.ሕ ክልላዊ መንግስት የወላይታ ዞን፣ በተለይም በሦስቱ የተመረጡ የዳሞት ጊሌ ማኅበረሰቦች መካከል የተካሄደ ነው፡፡ እነዚህ ጥናቱ የተካሄደባቸው ስፍራዎች ሥር ባላቸው እንደ እንሰት፣ ጎደሬ እና ስኳር ድንች ያሉ ተክሎችን በማብቀል እና የተመረጡ ጥራጥሬዎችን፣ ከእነርሱም በዋናነት በቆሎ እና ጤፍን በማብቀላቸው የግብርና ስርዓትን ይጋራሉ፡፡ ወላይታ ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ ባህላቸውም ቋንቋቸውም አንድ የሆነ የአንድ ጎሳ መኖሪያ ናት፡፡ በዚህ ስፍራ ከሚገኙት ማኅበረሰቦች

መካከል ሦስቱን መምረጣችን ጥናቱ መላውን ወላይታ እንዳይወክል የሚያግደው ቢሆንም፣ የግብርና ጥናት፣ የግብርና ምርምር፣ ብሔር፣ ባህል እና ቋንቋ በደምሳሳው አንድ ዓይነት መሆኑ ንጽጽር እንዲካሄድ ያስችላል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ የወላይታ ዞን ከአማካዩ የድህነት መጠን ከፍ ያለ የድህነት ሁኔታ የሚታይ እንዲሁም ከአማካዩ ያነሰ የመሬት ይዞታ መጠን ይታያል (Rahmato, 2007)፡፡ ወላይታ 8% የሚሆነው ሕዝብ ብቻ በከተማ አካባቢዎች የሚኖርባት ስለ ሆነች በአብዛኛው ገጠራማ ናት፣ ይህም አማካዩ በየዞኑ በገጠር የሚኖር ሕዝብ ብዛት 16% በሆነባት በኢትዮጵያ እጅግ አነስተኛ የከተማ ኗሪ ሕዝብ ብዛት ሲሆን፣ ከ1994 ሕዝብ እና ቤት ቆጠራ አንስቶ ይህ ብዛት ለውጥ ያሳየው በ1% ብቻ ነው (Rahmato, 2007)፡፡ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር የመጨመር ሁኔታ እንዲሁም አማካይ የሕይወት ዘመን ርዝማኔ መጨመሩ በወላይታ ለሚታየው የነፍስ ወከፍ የእርሻ መሬት መጠን መቀነስ በውርስ እና በመሬት መከፋፈል ምክንያት አስተዋጾ አድርጓል፡፡ ይህም ከእጅ ወደ አፍ ለሆነ መተዳደሪያ እንኳ ከሚበቃው ያነሰ የመሬት ይዞታ እንዲከተል አድርጓል፡፡ ሦስቱ ለጥናቱ የተመረጡ ማኅበረሰቦ የሚገኙበት የዳሞት ጊሌ ቀጠና ውስጥ የእርሻ መሬት ስፋት በአማካይ 0.25 ሄክታር[1] ሲሆን፣ አማካዩ 0.5 ሄክታር ከነበረበት ከ1989 እና 0.7 ሄክታር ከነበረበት ከ1976 ፈጣን ማሽቆልቆልን እንዳሳየ ያመላክታል (Rahmato, 1992, 2007)፡፡ ከታች በሚዘረዘረው ውጤት አማካኝነት እንደ ታየው፣ በሌሎች ጥናቶች (Guerin et al., 2013) እንደታየው ሁሉ ለብድር እና ባለዕዳነት መንስኤ የሆኑት መሠረታዊ የዕለት ተዕለት ፍላጎቶችን ማሟላት፣ የትምህርት እና የሕክምና ወጪን መሸፈን እንዲሁም የመተዳደሪያ አማራጮችን ለማስፋት መፈለግ አያሌ ቤተሰቦች የገንዘብ ብድር መውሰዳቸው ነው፡፡

የገንዘብ ብድር እና ዕዳ አነሳስ በገጠር አካባቢ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ በተለይም ከአለፈው ግማሽ ምዕተ-ዓመት ወዲህ፣ ከታየው የገንዘብ ምጣኔ ሀብት መስፋፋት ጋር የተያያዘ ነው (McCann, 1995)፡፡ አገልግሎቱን ለማግኘት ካለ የቅርበት ገደብ እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆነ የብድር አገልግሎት እንዳይስፋፋ ከሚያግደው ጠንካራ የፋይናንስ ደንብ የተነሳ አብዛኛው የገጠር የብድር ሂደት የሚካሄደው መደበኛ ባልሆነ መንገድ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደንቡ በአግባቡ ተፈጻሚ እንዳይሆን እንዲሁም፣ የወለድ መጠን ከፍተኛ እንዲሆን ከማድረጉም ባሻገር፣ እነዚህ አማራጮች ባንኮች አገልግሎት በማይሰጡባቸው አካባቢዎች ተፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶች እንዲገኙ ያደርጋል (Steel et al., 1997)፡፡ እንዲህ ያለው ቅንጅት አነስተኛ የብድር አገልግሎት ጥብቅ በሆነ መልኩ በደንብ በሚተዳደርባት ኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ ወሳኝ የሆነ የፖሊሲ መሻሻልን ይጠይቃል፡፡ በመንግሥት በኩል የባንክ አገልግሎቶችን በመላው የሀገሪቱ ገጠራማ አካባቢዎች በፍጥነት ለማስፋፋት እየተሞከረ ቢሆንም፣ ዓለም-አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምንም ዓይነት የፋይናንስ አገልግሎቶችን እንዳይሰጡ ማነቆ የመሆን ገጽታም አለው (Deribie et al., 2013)፡፡

## 4. የጥናቱ ዘዴ

መጠናዊ እና ኣይነታዊ ትንተና ዘዴዎችን በመጠቀም፣ ይህ ጥናት በገጠራማው ኢትዮጵያ ክፍል በሚኖሩት በአዴሮ፣ አዲ ኦፋ እና ቡጂ ማኅበረሰቦች ዘንድ ያለውን  አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች የዕዳ ሁኔታ ይቃኛል፡፡ እነዚህ ማኅበረሰቦች በማኅበረሰቦቹ ውስጥ እና መካከል ያለውን ልዩነት ለማነጻጸር እና ለማወዳደር ተብሎ በተለይ የተመረጡ ሲሆን፣ ሦስቱም ማኅበረሰቦች ከግብርና እና ስነ ምህዳር፣ ማኅበራዊ-ባህላዊ እና ፖለቲካዊ መቼት አንጻር ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ይህ ጥናት ቀድሞ በእነዚሁ ማኅበረሰቦች መካከል በተሠራ፣ የስፍራዎቹ ነዋሪዎችም ዕዳ ቸል የተባለ ጉዳይ እንደ ሆነ ከጠቆሙበት አሳታፊ እና በጋራ የተከናወነ የጥናት ፕሮጀክት ላይ ተመስርቶ ተስፋፍቶ የቀጠለ ጥናት ነው፡፡ እነዚሁ ነዋሪዎች እንዳመላከቱት ዕዳ ንብረት የማፍራት አቅማቸውን ይገድባል፣ እንዲሁም ተጨባጭ መጠን ያለው ቀጥተኛ(ወለድ ከመክፈል የተነሳ ገቢ ይመናመናል) እና ተዘዋዋሪ (የአቅርቦት እጥረት ከመኖሩ የተነሳ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት አዳጋች ይሆናል) ፈታኝ ሁኔታን ያስከትላል፡፡ ነዋሪዎቹ በተለይ በዕዳ ላይ ያተኮረ ጥናት ቢከናወን እንደሚጠቅማቸውም አመላክተዋል፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ የቤት ለቤት መጠይቅ ዳሰሳ እና የተመረጠ ቡድን ውይይት የተካሄዱ ሲሆን፣ በውይይቱ ላይ የማኅበረሰቡ አባላት ያቀረቧቸው መረጃዎች ተሰልተው የተካተቱ ሲሆን፣ የማጠቃለያውን ጠቃሚነት የተመለከተ ውይይት ተካሂዷል፣ ተጨማሪ ኣይነታዊ ዐውድም ተካትቷል፡፡

የቤት ለቤት መጠይቅ ዳሰሳው በሦስቱም ማኅበረሰቦች መካከል ተለይተው በተመረጡ መንደሮች ውስጥ ተካሂዷል፡፡ በሌሎች መንደሮች በኩል አልፎ ሳይሆን ቀጥታ የመስኖ አገልግሎት በማግኘት መስፈርት የተመረጡ ሲሆን፣ በአዴሮ እና አዴ ኦፋ፣ በተመረጠው መንደር መጠይቁ የተሞላባቸው ቤቶች ብዛት 221 ሲሆን፣ በቡጂ ደግሞ 79 ቤቶች ተመርጠዋል፡፡[2]

የመጀመሪያው ማኅበረሰብ የሆነው አዴሮ ከቦዲቲ ከተማ አቅራቢያ የሚገኝና በእርሻ የሚተዳደር ሲሆን፣ ለባንክ፣ ገበያ፣ ትምህርት ቤቶች እና የጤና ክብካቤ አገልግሎት የተሻለ ቀረቤታ አለው፡፡ ከከተማው ቅርበት የተነሳ የአዴሮ ነዋሪዎች ምርቶቻቸውን ወደ ገበያ

---

[1] ከዳሞት ጊሌ ቀጠና የግብርና ቢሮ በ2015 መረጃ ላይ ተመስርቶ በጁን 2015 የተገኘ መረጃ ነው፡፡

[2] የተመረጡት መንደሮች ይፋዊ የሆነ አስተዳደራዊ ድንበር የሌላቸው ስለ ሆነ አጠቃላይ አባላት ቁጥር የማይታወቅ ቢሆንም፣ አኗኗራቸው መንግሥት ለእያንዳንዱ መንደር አገልግሎት ለመስጠት እንዲያመቻቸው የከፋፈላቸው ስለ ሆነ፣ የማኅበረሰቡ አባላት እያንዳንዱ መንደር የት እንደሚገኝ ያውቃሉ፡፡

ለመሸጥ ወይም የዕለት አልያም ወቅታዊ የጉልበት ሥራ ለማግኘት ይችላሉ፡፡ ሁለተኛው በጥናቱ የተሳተፈ ማኅበረሰብ፣ አዳ አፋ ደግሞ አጎራባች እና ጭቃማ በሆነ መንገድ 15 ኪ.ሜ ያህል ተጉዞ የሚደረስበት ነው፡፡ አዳ አፋ የተመረጠው በሁለቱ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው በግብርና የሚተዳደሩ ማኅበረሰቦች መካከል ያለውን የመልከዓ-ምድራዊ መገኛ እና ለእነዚህ አገልግሎቶች ያላቸውን ቅርበት ለማነጻጸር ስለሚያመች ነው፡፡

ሦስተኛው ማኅበረሰብ፣ ቡጂ ደግሞ መሀል ለመሀል የሚያቋርጠው ዋና አስፋልት መንገድ ይገኝበታል፡፡ በከተማ አቅራቢያ የሚገኝ ባይሆንም፣ መንገዱ በተወሰነ ደረጃ የተሻለ የአገልግሎት አቅርቦት እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡ ቡጂ፣ ከቡጂ ውስጥም ተለይቶ የተመረጠ ክፍል በጥናቱ እንዲጠቃለል የተደረገው እንደ እርዳታ-ልማት ፕሮጀክት ሆኖ ከአስር ዓመታት በፊት ከተሠራው መሠረተ ልማት የተነሣ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት ቤተሰቦች የመስኖ አገልግሎት እንዲያገኙ በማስቻሉ ሕይወታቸውን እንዲለውጡ አስችሏቸዋል፡፡ ቀድሞ በዝናብ መጣል ላይ ተወስኖ ይከወን የነበረው የግብርና ሥርዓት መደበኛ ያልሆነውን የዝናብ ሁኔታ መቋቋም የሚችሉ ወይም ብዙ ውሀ የማያስፈልጋቸው ተክሎችን መኸር በዓመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ያህል ብቻ ነው የሚያስገኘው፡፡ በመስኖው አማካኝነት ቤተሰቦች ሦስት ወይም አራት መኸሮችን እንዲያገኙ የሚያስችላቸው ሲሆን፣ የሚያበቅሉትን ዓይነት ከማብዛታቸው አልፎ አንዳንድ ቤተሰቦች ቀድሞ ለምግብነት የማይውሉ የነበሩ አትክልቶችን ማብቀልም ጀምረዋል፡፡ ቡጂ በዚህ ጥናት ውስጥ መካተቷ ይህኛው አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች ካላቸው ተነጻጻሪ ጠንካራ ምጣኔ ሀብታዊ አቅም እና የምግብ ዋስትና ሁኔታ አንጻር የብድር ልማዳቸው ከሌሎቹ ሁለቱ ማኅበረሰቦች ጋር እንዴት እንደሚነጻጸር ለማስላት ነው(Cochrane and Gecho, 2016)፡፡

በአጠቃላዩ በሦስት መቶ መጠይቆች አማካኝነት ቅኝት ተካሂዷል፡፡ በሦስቱም ማኅበረሰቦች ውስጥ በተናጠል 200 ቤቶች ይገኛሉ በሚል መላ ምት፣ በቡጂ በሰፊ ሁነታ ከመስኖ ፕሮጀክቱ ጋር ከተገናኙ ደ10 ቤቶች መካከል በ79 ላይ ቅኝቱ ተካሂዷል (ከአጠቃላይ ቤቶች 56%)፡፡ በአዴሮ በ96 ቤቶች ላይ ቅኝቱ የተካሄደ ሲሆን፣ ይህም ከአጠቃላይ የአዴሮ ማኅበረሰብ ውስጥ ግማሽ ያህሉ ይሆናል (48% ገደማ)፡፡ በአዴ አፋ ደግሞ በ125 ቤቶች ላይ ቅኝቱ ተካሂዷል ይህም ከአጠቃላይ ማኅበረሰቡ ውስጥ 63% ያህል ነው፡፡ መረጃውን የሰበሰቡት ሦስት ሠራተኞች ከዚህ ቀደም የዳሰሳ ጥናቶችን የማካሄድ ልምድ ያላቸው ሲሆን፣ የአካባቢውን ቋንቋ ይናገራሉ፡፡ የገንዘብ አቅም ሁኔታን ላለመግለጥ አስበው የማኅበረሰቡ አባላት እንዳይቸገሩ፣ የተዛባ መረጃ እንዳይገኝም ሲባል ዳሰሳውን ያካሄዱት ሰዎች ከሦስቱ ማኅበረሰቦች ውጪ መሆናቸውን አረጋግጠናል፡፡ ምክንያቱም፣ ሌሎች ተመራማሪዎች እንዳመላከቱት ገበሬዎች የራሳቸው ማኅበረሰብ አባል ከሆኑ ሰዎች ጋር ስለ ገንዘብ ጉዳይ ለመወያየት ፈቃደኛ አይደሉም (Sana et al., 2012)፡፡ እነዚህን የዳሰሳ መጠይቆች ተሳታፊዎች የሞሉት በፈቃደኝነት ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው ተሳታፊዎች ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆናቸውን በቃላቸው አረጋግጠዋል፡፡ መረጃ በተሰበሰበበት ሂደት ወቅት የተሳታፊዎ ማንነት እንዳይገለጥ የተደረገ ሲሆን፣ የተሳታፊዎች ስምም ሆነ የቤት ቁጥር አልተካተተም፡፡ መረጃውን በማሰናሰል ወቅት የማኅበረሰቦቹ ልዩነት የብድር እና የእዳ ሁኔታ ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንዳሳደረ ለማየት ሲባል የዳሰሳው ውጤት ከተመሳሳይነት እና ከልዩነት አንጻር ለማወዳደር እና ለማነጻጸር እንዲቻል በመገኛ ተለይቶ ተሠርቷል፡፡ አጠቃላይ እንዲሁም በመገኛ ተለይቶ የተሠራው ውጤት መረጃውን ከማስላት በኋላ በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ውስጥ በተካሄደው በተመረጡ ርዕሶች ላይ የተካሄደ የቡድን ውይይት ወቅት  የየማኅበረሰቡ አባላት ራሳቸው ውጤቶቹን እንዴት እንደ ተገነዘቧቸው እና እንደሚገልጿቸው አይቶ አውድ ለማስያዝ ተሞክሯል፡፡

## 5. ከዳሰሳ መጠይቆቹ የተገኘ ውጤት

### 5.1. የብድር ድግግሞሽ

ጥናት ከተካሄደባቸው 300 ቤቶች መካከል እያንዳንዱ ቤተሰብ ካለፉት አምስት አመታት ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ ብድር ተበድሯል፡፡ አንድ ቤተሰብ በአማካይ ብድር የወሰደባቸው ጊዜያት በአማካይ 2.75 ሲሆኑ፣ በሦስቱ ማኅበረሰቦች መካከል እምብዛምም መለያየት አልታየም (በቡጂ 2.5፣ በአዴሮ 2.8 እና በአዳ አፋ 2.9)፡፡ ከአገልግሎት ተደራሽነት አንጻር ማኅበረሰቦቹ ልዩነት ስላላቸው ይህ ውጤት ያልተጠበቀ ሆኗል፡፡ እንዲሁም የመስኖ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑትም ሆነ ራቅ ባለው ገጠራማ ስፍራ የሚኖሩት ማኅበረሰቦች የሚወስዱት የብድር መጠን ተመሳሳይነት ያለው መሆኑ ያልተጠበቀ ውጤት ነው፡፡  ይህ መላ ምት የተነሳው አበዳሪዎች የተሻለ ንብረት እና ገቢ ላላቸው ጠያቂዎች ቅድሚያ እንደሚሰጡ ከግምት በማስገባት ነው፡፡ ብዛታቸው አነስተኛ ቢሆንም በቡጂ የመስኖ አገልግሎት ተጠቃሚ ከሆኑት ማኅበረሰቦች መካከል ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ብድር የወሰዱ ቤተሰቦች ብዛት 70% ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ የተሻለ የገንዘብ ዋስትና እና/ወይም ንብረት ያላቸው ቤተሰቦች፣ አነስተኛ ንብረት ካላቸው ጋር ሲተያዩ የበለጠ ባለ ዕዳ ሆነው ከተገኙበት በታይላንድ ከተካሄደው ጥናት ጋር ተነጻጻሪ ነው (Nuansoi, 2013)፡፡ በወላይታ የሚታየው የብድር አሰናሰል እንዳመላከተው ብድር ከአስቸጋሪ ጊዜዎች ጋር፣ በተለይም ከከፋ ድህነት እና የምግብ ዋስትና ማጣት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እንዲህ ያሉ ብድሮች የሚወሰዱት መኸር በተመናመነበት የእጦት ጊዜ ላይ ነው፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ንብረት የሚሸጥ ቢሆንም፣ አነስተኛ ብድሮች ገበሬዎች ጠቃሚ የገቢ እና የሥራ ምንጭ አድርገው የሚቆጥሯቸውን እንደ ቁም ከብት ያሉ ንብረቶችን ለማቆየት ይወሰዳሉ፡፡  ከሦስቱ ማኅበረሰቦች መካከል ራቅ ያለው ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የምግብ ዋስትና ማጣት፣ ከፍተኛ የሆነ የሙያ ባለቤት ያልሆነ ሕዝብ ፍልሰት እንዲሁም በገበያ የሚሸጡት የእህል መጠን አነስተኛ መሆን የሚስተዋልበት ነው (Cochrane and Vercillo,

2017)፡፡ እንዲያም ሆኖ፣ አማካይ የብድር መጠን ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም መስኖው የተለየ ጥቅምን እንደማያስገኝ የሚያመላክት ቢሆንም፣ የመረጃው ውጤት የተለየ ውጤት እንደሚጠቁም ቀጥለን የምንትነትን ይሆናል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት፣ አብላጫ ቁጥር ያላቸው ቤተሰቦች (90%) ከ2- 4 ጊዜ ያህል ብድር የወሰዱ ሲሆን፣ ብድር ከወሰዱት መካከል 8% የሚሆኑት ከአምስቱ አመታት መካከል ብድር የወሰዱት አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ 2% ደግሞ ከአምስቱ ዓመታት ውስጥ በእያንዳንዱ ዓመት አንድ ጊዜ፣ በአጠቃላይ አምስት ጊዜ ብድር ወስደዋል፡፡ የብድር ድግግሞሹ በከፊል በኢትዮጵያ ካለው የግብርና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ እንደ ማዳበሪያ ያሉ ግብአቶችን እያንዳንዱ ቤተሰብ ሊገዛ ካልቻለ የሚያገኘው በብድር ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ ግብአቶችን በመግዛት ሂደት ውስጥ የሚፈጠር ከግብርና ጋር የተያያዘ ዕዳ በሀያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በዓለም ዙሪያ እየታየ ያለ ፈታኝ ሁነታ ስለ ሆነ፣ ኢትዮጵያን ብቻ የሚመለከት አይደለም (Estenson, 1987; McMichael, 2013)፡፡ በቡድን ውይይት ወቅት ገበሬዎቹ እንደ ገለጹ፣ በአነስተኛ የብድር ተቋማት አማካኝነት የሚሰጥ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ባለ መሆን ከመንግሥት ባለ ዕዳነት መሸሽን ይመርጣሉ፡፡ ተሳታፊዎቹ እንደ ገለጹት ለአጭር ጊዜ ተመድቦ ከመንግሥት የሚወሰድ ብድር መሬታቸውን በዕዳ ሊያስወርስ የሚችል ሲ ን፣ መደበኛ ካልሆኑ አበዳሪዎ የሚገኝ ብድር ግን ሊራዘምና በሕይወት ዘመን ባለ ዕዳነት ሊከማች ይችላል፡፡ መደበኛ ያልሆነ ብድር በመደበኛ መንገድ መሬት እንዲወረስ አያስችልም፣ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሕግ የገጠር የግብርና መሬት ከግለሰብ ወደ ግለሰብ በሽያጭ ወይም በዝውውር እንዲተላለፍ አይፈቅድም፡፡ እንዲያም ሆኖ መደበኛ ያልሆነ የመሬት ዝውውር ይካሄዳል (Holden et al., 2016)፡፡ ገበሬዎች ከመንግሥት በብድር ግብአቶችን በሚቀበሉበት ወቅት የመሬት ባለ ይዞታነት የምሥክር ወረቀታቸውን ያስይዛሉ፡፡ ድጎማ የሚደረግባቸው የመንግስት አቅርቦቶች ዝቅተኛ በሚሆኑበት ወቅት ግብአቶች የሚገኙት ከገበያ ስለ ሆነ፣ ድሀ የሆኑት የማኅበረሰቡ አባላት በሁለቱም ሁኔታዎች ውስጥ ቢሆኑ ብድር ማግኘት ግድ ይሆንባቸዋል፡፡ በወላይታ ለብዙ አስርት ዓመታት የግብአቶች አቅርቦት ተጨባጭ የሆነ መዋዠቅን አሳይቷል (ምስል 1.ን ይመልከቱ)፡፡

**ምስል 1. በወላይታ ዞን መንግስት የሚያካሂደው የማዳበሪያ ስርጭት፣ 1970 እስከ 2000 ድረስ የተመረጡ ዓመታት (በ50 ኪ.ግ. ከረጢቶች)**




ከሚያስከትለው አስጨናቂ ውጤት የተነሳ ቤተሰቦች በተቻላቸው መጠን መደበኛ ከሆነ ዕዳ ራሳቸውን ይጠብቃሉ፣ በተደጋጋሚ ብድር የሚወስዱትም ከኑሮ አስገዳጅነት የተነሳ ነው፡፡ በተደረገው ዳሰሳ የተገኘው መረጃ በቡድን ውይይቶች ወቅ ከተገኘው ገለጻ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን፣ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ የተወሰዱት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ብድሮች እና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ክስተቶች የተስተዋሉት ቤተሰቦች ዕዳቸውን መክፈል ባልቻሉባቸው ጊዜያት መሆኑ (r = 0.65)፣ በበለጠ ድግግሞሽ ብድር የሚወስዱት

ሰዎች ናቸው የመክፈል አቅም የሌላቸው፡፡ በተጨማሪም፣ በብድር መጠን እና ብድርን በመክፈል ያለመቻል መካከል ያለው ግንኙነት የሚያሳየው ደካማ አዎንታዊ ውጤትን መሆኑ (r = 0.29)፣ ዕዳን መክፈል ያለ መቻል ከተበደሩት መጠን ይልቅ በተደጋጋሚ ከመበደር ጋር ተያያዥነት እንዳለው ያመላክታል፡፡ የቤት ለቤት ዳሰሳው ዕዳ ለመክፈል ያልተቻለባቸውን ዓመታት ነጥሎ አውጥቶ የማያሳይ ሲሆን፣ ዕዳ ለመክፈል ያልተቻለበትንም ምክንያት አያትትም፡፡ ስለዚህ፣ እነዚህ መንስኤና ውጤቶች ያላቸውን ተያያዥነት በበለጠ ለመቃኘት አያስችልም፡፡ ተያያዥነታቸውን የመተንተን ገደብ እንዳለ ብንገልጽም፣ እነዚህ ግኝቶች በተለይም ዕዳን ለመክፈል ያለመቻልን ምክንያት ለማጥናት ለሚነሱ የወደ ፊት ምርምሮች አጋዥ ይሆናል፡፡ ተያያዥነት ያላቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄዱ ጥናቶች እንዳሳዩት ለመበደር ምክንያት (በሕይወት መቆየት ተገቢውን የሥራ መዋዕለ ነዋይ ማፍሰስ ጋር ሲነጻጸር) ከፍተኛ አቅም እና ዝቅተኛ የግብርና አቅም ባላቸው አካባቢዎች እንደ ታየው፣ ዝቅተኛ የግብርና አቅም ባላቸው አካባቢዎች የብድር ሁኔታ ከአምራችነት ጋር ተያያዥነት አያሳይም፣ ስለዚህም በእነዚህ ቦታዎች የሚታየው ሕይወትን ለማቆየት የሚወሰድ የብድር አገልግሎት ነው (Ali and Deininger, 2014)፡፡

### 5.2. የብድር መጠን

ጥናቱ በተካሄደባቸው ሦስት ማኅበረሰቦች ዘንድ እንደ ታየው የብድሩ መጠን ከ100 ብር እስከ 10,000 ብር የሚደርስ ነው፡፡ ዝቅተኛ ብድር የሚካሄድባቸው ሁኔታዎች ቤተሰቦች ምግብ የሚያጡበት እና አስፈላጊ የምግብ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስችል ድጎማ የሚፈልጉባቸው ጊዜያት ሲሆኑ፣ ከፍተኛ መጠን ያለው የብድር መጠን የሚስተዋለው ደግሞ እንደ በአህያ የሚጎተት ጋሪ ወይም ሞተር ሳይክል ያሉ አጋዥ ግብአቶችን ለመግዛት ወይም እንደ ሠርግ ያሉ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ ስነ ስርዓቶችን ለማከናወን ነው፡፡ በአንድ ዓመት ውስጥ ለብድር የዋለው አማካይ የገንዘብ መጠን 1717 ብር ነው፡፡ ዐውዱን ለመገንዘብ እንዲያስችል፣ 50 ኪ.ግ. ከረጢት ማዳበሪያ ዋጋው 700 ብር እንደሆነ፣ ይህም ከአማካዩ አመታዊ የብድር መጠን በ40% እንደሚበልጥ ይታያል፡፡ በእነዚህ ማኅበረሰቦች ውስጥ የሚኖሩ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች በተለይም የዚህ የማዳበሪያ ከረጢት ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ከገቢ እና አስፈላጊዎቹን አቅርቦቶች ከመግዛት እና ብድርን ከመክፈል ጋር በተያያዘ ሴቶች ለማገዶ የሚሆን እንጨት ወይም ሣር በመሰብሰብ በአቅራቢው ባለ ገበያ የሚሸጡ ሲሆን፣ ቀኑን ሙሉ ሲለፉ ውለው የሚያገኙት ገንዘብ ከ10-15 ብር የሚደርስ ነው፡፡ ነገር ግን፣ የማገዶ እንጨት እና ሣር እንደ መሰብሰብ ያሉ የቀን ሥራዎች ዕዳን ለመክፈል ታስቦ የሚሠሩ ሳይሆኑ አማራጭ ሲታጣ የሚገቡባቸው ናቸው (Cochrane and Gecho, 2016)፡፡ እነዚህን ድምሮች በይበልጥ ዐውድ ውስጥ አስገብቶ ለማሳየት እንዲቻል የሚከተሉትን እንመልከት፡፡ እንደ ወባ ሕክምና ያሉ ድጎማ የሚደረግባቸው መሠረታዊ የጤና ክብካቤዎች ዋጋ ከሁለት ቀናት የቀን ሥራ ደመወዝ ጋር እኩል ነው (30 ብር)፡፡ ብድርን መልሶ ለመክፈል ሲባል ገበሬዎች ለሽያጭ የሚሆኑ ተለይተው የሚታወቁ ዘሮችን (በዚህኛው ወቅት ጤፍ እና በቆሎ) የሚዘሩ ሲሆን፣ ለቤት ውስጥ ፍጆታ ደግሞ ሌሎች ተክሎችን (እንደ እንሰት፣ ጎደሬ እና ድንች ያሉ) ይተክላሉ፡፡ ያለ ጊዜው የመጣ፣ የዘገየ፣ በቂ ያልሆነ ወይም ከመጠን ያለፈ ዝናብ በተገኘባቸው ዓመታት አጠቃላዩ ሰብል ስለሚወድም ዕዳን ለመክፈል ያለ መቻልን ያስከትላል፡፡ እንዲህ ያለ ለመገመት የሚያዳግት የዝናብ ሁኔታ በወላይታ በተደጋጋሚ የሚከሰት ነው (Cochrane and Gecho, 2016)፡፡ በተከታታይ ዓመታት ዝናብ በሚታጣ ጊዜ (ገሚስ-)ቋሚ የባለ ዕዳነት ሁኔታ ይከተላል፣ ይህም የመሬት ይዞታን ማጣትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

ዝቅተኛ አማካይ የብድር መጠን የታየው የመስኖ መሠረተ ልማት ተጠቃሚ በሆነው በቡጂ ማኅበረሰብ መካከል ሲሆን (1469 ብር)፣ ከፍተኛው አማካይ የብድር መጠን ደግሞ ለከተማ ቀረብ ብሎ በሚገኘው በአዴሮ ማኅበረሰብ ውስጥ ታይቷል (1998 ብር)፡፡ ይህም ከፍተኛ የብድር መጠን ለመውሰድ ያለመቻል ተደርጎ ሊተረጎም ቢችልም፣ ዝቅተኛው አማካይ የብድር መጠን የሚታየው በዚሁ ብዙ ቤተሰቦች ከአምስት ዓመታት ውስጥ በአንዱ ብቻ በከፍተኛ ሁኔታ በተበደሩበት ማኅበረሰብ መካከል የሚታይ መሆኑ፣ እንዲሁም የቤተሰቦች ብዛት መጠን ሲጨምር እና የምግብም ሆነ የገንዘብ ዋስትና ሲገኙ የብድር ሁኔታ በድግግሞሽም ሆነ በአጠቃላይ መጠን ሊቀንስ ይችላል ከሚለው መላ ምት ጋር የሚሄድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እነዚህ ውጤቶች Gray and Dowd-Uribe (2013) በቡርኪና ፋሶ በአንጻራዊነት ባለጠጋ የሆኑት በችግር ጊዜ ከዕዳ ነጻ ሆነው መገኘታቸውን ካሳየበት የጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በአንጻሩ፣ አስቀድሞ ከተመሳከሩ የጥናት ጽሑፎች እንደሚጠበቀው (Gecho, 2014; Handino, 2014; Tesfamariam, 2012)፣ ከፍተኛው የብድር መጠን የተገኘው በከተማ አቅራቢያ ባለው የአዴሮ መንደር ነው፡፡

የማኅበረሰቡ አባላት ለሁኔታው ለገበያ ቅርብ መሆንን ጨምሮ ልዩ ልዩ ምክንያቶችን ዘርዝረዋል፡፡ ገበያዎች በአቅራቢያው በሚገኙበት ሁኔታ፣ ገበሬዎች ለሥራ የሚያስፈልጓቸውን አቅርቦቶች ለመግዛት እንዲበረታቱ ስለሚያደርግ፣ የፍራፍሬ ዛፎች፣ በተለይም የአቮካዶ ዘር፣ እንዲሁም ለገበያ የሚውሉ እንደ ቡና ያሉ ዘሮችን እና ለእነርሱ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ይገዛሉ፡፡

ሌላው በአዴሮ በተካሄደው የቡድን ውይይት ወቅት የቀረበ ምክንያት ብድር ሊገኝ የሚችልባቸው ቦታዎች መብዛት ሲሆን፣ በአንድ ዓመት ብቻ ከተለያዩ ቦታዎች ብዙ ብድር ለመውሰድ ያስችላል፡፡ በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ አንድ ቤተሰብ በተደጋጋሚ ብዙ ብድሮችን የመውሰዱን ሁኔታ በመጠይቅ አማካኝነት የተገኘው መረጃ የሚደግፈው በከፊል ነው፤ ከቡጂ (13%) ጋር ሲነጻጸር፣ አዴሮና አዳ አፋ ከአንድ ጊዜ በላይ የመበደር ሁኔታቸው የሚበልጥ ነው (20%)፡፡ አማካይ የብድር መጠን በአዴሮና በአዴ አፋ በልጦ የተገኘ

መሆኑ፣ በአዴሮ ለታየው ከፍተኛ አማካይ የብድር መጠን የማኅበረሰቡ አባላት የሰጡት ገለጻ ደጋፊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ በ5-ዓመታት ጊዜ ውስጥ በብድር ላይ የዋለ አማካይ የብድር መጠን 8,820 ብር ሲሆን፣ ዝቅተኛው አማካይ መጠን በቡጂ (7,305 ብር)፣ ከፍተኛው ደግሞ በአዴሮ (10,749 ብር) ታይቷል፡፡ ይህም ከአማካይ ዓመታዊ ግኝት ጋር ወጥነት ያለው ነው፡፡

### 5.3. ዕዳን መክፈል

አያሌ ቤተሰቦች እዳቸውን በወቅቱ ለመክፈል ያልቻሉበት ሁኔታ ገጥሟቸዋል፡፡ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ቤተሰቦች በአማካይ 2.4 ጊዜ ያለባቸውን እዳ እንደሚፈለግባቸው ለመክፈል ሳይችሉ ቀርተዋል (በቡጂ 2.2. እና በአዴሮና አዳ ኦፋ በሁለቱም 2.5)፡፡ ነገር ግን፣ ከግማሽ የሚበልጡት ቤተሰቦች (51%) በዚህ የአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሁለት ጊዜ ወይም ከዚያ ላነሰ ጊዜ ዕዳን በተገደበው ጊዜ ለመክፈል ያልቻሉ ስለ ሆነ፣ ያለመክፈል ሁኔታው ስርጭት ኢ-እኩልነት የተስተዋለበት ነው፡፡ አንዳንድ ቤተሰቦች፣ በአንድ ዓመት ውስጥ ዕዳን በተገደበው ጊዜ በተደጋጋሚ ለመክፈል ሳይችሉ የቀሩ ሲሆን፣ ባለፉት አምስት አመታት ውስጥ አንድ ቤተሰብ ዕዳን ለመክፈል ያልቻለበት ጊዜ ብዛት ከፍተኛው ስምንት ጊዜ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ጥናቱ ባተኮረባቸው ያለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በክልሉ ከፍተኛ የምግብ እጥረት የተስተዋለበት ሁኔታ መከሰቱ (2011-2012)፣ በድንገተኛ ክስተቶች ወቅት የሚቀርበውን የምግብ እርዳታ እንዲቀርብ አስገዳጅ አድርጎት ተገኝቷል፡፡ በተጠቀሱት ዓመታት፣ ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ አብዛኛዎቹ ቤተሰቦች ብድር የተበደሩ ሲሆን፣ የጠበቁትን የግብርና ምርት ለማግኘት ባለመቻላቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ዕዳቸውን ለመክፈል አዳግቷቸዋል፡፡ ይህም ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ፣ አንድ ቤተሰብ ብቻ ዕዳውን መልሶ ለመክፈል የቻለበትን ምክንያት በሚገባ ይገልጸዋል፡፡ ለሁሉም ነዋሪዎች 2011 እና 2012 እጅግ ፈታኝ ዓመታት የነበሩ ሲሆን፣ መበደር መስፋፋቱንና 49% የሚሆኑት ቤተሰቦች ባለፉት አምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ለሦስት ወይም ከዚያ ለሚበልጡ ጊዜ ያት ዕዳቸውን ለመክፈል ያለመቻላቸውን ማጤን ያስፈልጋል፡፡ ከፍተኛ የሆነው ዕዳን መልሶ ለመክፈል ያለ መቻል ሁኔታ ከብድር ምክንያት (ሕይወት ለማቆያ እንዲሁም ለሥራ የሚያስፈልጓቸውን ግብአቶች ለመግዣ) አንጻር ሊገለጽ የሚችል ሲሆን፣ በአንጻራዊነት በድህነት የሚኖሩት ቤተሰቦች በተደጋጋሚ የሚበደሩ ሲሆን፣ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ሲቸገሩ ዕዳቸውን መልሰው ለመክፈል ሳይችሉ ይቀራሉ፡፡

ከፍተኛ መጠን ያለው ዕዳን ለመክፈል ያለ መቻል ድግግሞሽ ግለሰቦችም ይሁኑ ተቋማት መጀመሪያውኑ ለምን ለመበደር ይነሳሳሉ የሚል ጥያቄን ያስነሳል፡፡ ዕዳን ለመክፈል ያለ መቻል ቀድሞ ከነበሩበት ያነሰ የኑሮ ሁኔታ ላይ ስለሚጥል፣ ይህ ጥያቄ ጠቃሚ ማብራሪያን ይፈልጋል፡፡ ዕዳን ለመክፈል ያለ መቻል ማለት፣ ዕዳው ስምምነት ላይ በተደረሰበት መጠን፣ ስምምነት በተደረገበት የጊዜ ገደብ ለመክፈል ያለ መቻል ማለት ነው፡፡ ውጤቱም የሚወሰነው በብድር ሰጪው አካል ሲሆን፣ የመቀጮ መልክ ይኖረዋል፡፡ ከገንዘብ ቅጣት በተጨማሪ፣ መደበኛ ያልሆኑ አበዳሪዎች ከተበዳሪዎቻቸው እንደ የቁም ከብት ያሉ ንብረቶችን ገንዘባቸው እስከሚከፈላቸው ድረስ ሊወስዱ ይችላሉ (በወሰዱበት ጊዜም ንብረቶቹ ለአበዳሪዎቹ ግልጋሎት እና ጥቅም የሚሰጡ ይሆናሉ)፡፡ ኢ-መደበኛ በሆነው ስርዓት ውስጥ፣ ገበሬዎች ዕዳቸውን ለመክፈል አልቻሉም ተብሎ አይተዉም፡፡ በመደበኛው ስርዓት ውስጥ ዕዳን ለመክፈል ያለ መቻል ንብረት እና መሬትን ማጣትን የሚያስከትል ሲሆን፣ ንብረቱን ሁሉ መንግሥት የሚወርሰው ይሆናል፡፡

የዳሰሳ ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት ግን፣ ሁሉንም ውዝፍ እዳዎች በዚያው ዓመት ውስጥ ከፍሎ የመጨረስ ከፍተኛ መተማመን (67%) የተስተዋለ ቢሆንም፣ ይህ መጠን ከቡጂ (73%) እና አዴሮ (72%) ይልቅ በአዳ ኦፋ (61%) ዝቅተኛ ሆኖ ታይቷል፡፡ በአንጻራዊነት ዕዳን የመክፈል ከፍተኛ የራስ መተማመን መታየቱ ምናልባትም መኽሩ እንደታሰበው ባይሆን እንኳ፣ ራቅ ባለው ገጠራማ አካባቢ እምብዛምም የማይገኝ በጉልበት ሥራ የመሰማራት ዕድል ከመኖሩ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም፣ ቤተሰቦች አቅርቦቶቻቸውን ሊያሚጥጡና ዕዳ የመክፈል አቅማቸውን ሊያዳክሙ የሚችሉ ድንገተኛ ክስተቶችን የማያስቡ መሆናቸው አስተዋጾ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ቤተሰቦች በከፍተኛ ሁኔታ ዕዳን ለመክፈል ያለመቻላቸው እንደሚያሳየው ከሆነ፣ ይህ ከእውነታው ጋር ያልተመጣጠነ የራስ መተማን ሊሆን ይችላል፣ እንዲሁም ያልተቋረጠው ዓመታዊ የብድር ሁኔታ እንደሚያሳየው ቤተሰቦች ለሥራ የሚያስፈልግን ግብአት ለማዘጋጀት ከሚበደሩ ይልቅ፣ ሕይወትን ለማቆየት እንደሚበደሩ ግልጽ ነው፡፡ አንዳንድ ቤተሰቦች ባለ ዕዳነትን ለመቅረፍ አያሌ ዓመታትን ሊፈጅባቸው የሚችል ሲሆን፣ ብዙ ዓመታት እና ከል ልዩ ቦታ የሚገኝ አያሌ ብድር ማግኘት ያስፈልጋቸዋል፣ አንዳንዶች ደግሞ ፈጽመው ከባለዕዳነት ሊወጡ አይችሉም፡፡ በረዥም ጊዜ እንደ ታየው ይህ ጥናት የሚያመላክተው አብዛኛዎቹ ቤተሰቦች በተወሰነ መጠን ባለ ዕዳነትን የሚያበረታታ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ቢኖሩም ራሳቸውን ከዕዳ ለማላቀቅ ችለዋል፡፡ Rahmato (2007) እንዳሳየው በወላይታ የሚኖሩ ቤተሰቦች ጥቂትም ቢሆን የኑሮ ነውጥን ለመቋቋም የሚያስችል አቅም የሌላቸው መሆኑ፣ የብድር እና ባለዕዳነት አዙሪት ውስጥ ያስቀራቸዋል፡፡

ሰንጠረዥ 1. የብድር ምንጮች ድግግሞሽ እና የወለድ መጠን መነሻና መድረሻ

| ምንጭ | የወለድ መጠን | አዴሮ (%) | አዳ አፋ (%) | ቡጂ (%) | አጠቃላይ (%) |
|---|---|---|---|---|---|
| ማኅበራት | 15 | 29 | 27 | 27 | 27 |
| አካባቢያዊ አበዳሪ | 3-50 | 10 | 19 | 11 | 14 |
| አነስተኛ የብድር ተቋም | 15 | 34 | 38 | 31 | 34 |
| ሌሎች | 2-15 | 23 | 9 | 25 | 18 |
| ነጋዴዎች | 2-8 | 5 | 7 | 5 | 6 |

### 5.4. የብድር ምንጮች

የብድር ምንጮችን ብዝሀነት ለመፈተሽ እያንዳንዱ ቤተሰብ የብድር ምንጫቸውን እንዲያመለክቱ ተጠይቀው ነበር፡፡ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ከአማካዩ መካከል 2.75 ብድሮች የወሰዱት በአማካይ ከ1.7 ልዩ ልዩ ምንጮች ነው፡፡ የብድር ምንጭ አይነቶች ልዩ ልዩ ሆነው የተገኙ ሲሆን፣ በብዛት መንግሥት የሚያስተዳድራቸው የአነስተኛ ብድር ተቋማት፣ ሕብረት ሥራ ማኅበራት፣ አካባቢያዊ አበዳሪዎች፣ ነጋዴዎች፣ የቤተሰብ አባላት እንዲሁም በማኅበራዊ ትስስር አማካኝነት የተገኙ አማራጭ ምንጮች ተጠቅሰዋል፡፡ በአጠቃላዩ ተመሳሳይ አካሄድ ቢታይም፣ የብድር ምንጮች እንደየማኅበረሰቡ ሲለያዩ ታይቷል (ሰንጠረዥ 1ን ይመልከቱ)፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ ወቅት 'ቤተሰብ' እንደ ብድር ምንጭ ያልተጠቀሰበት ምክንያት፣ ከቤተሰብ የሚገኝ ገንዘብ 'ብድር' እንደ ሆነና እንዳልሆነ ለመለየት ከመቸገር የተነሣ ነው፡፡ በዘመዳሞች መካከል የሚደረግን ብድር ባህሪ፣ መጠኑን እና ድግግሞሹን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ተጨማሪ ጥናት ያስፈልጋል፡፡

እንደ ብድር ድግግሞሽ ሁሉ፣ የምንጮች ቁጥርም በሦስቱ ማኅበረሰቦች መካከል እምብዛምም የተለያየ አይደለም (1.7 በቡጂ፣ 1.9 በአዴሮ እና 1.5 በአዳ አፋ)፡፡ ለጥናቱ ተብሎ በተዘጋጀው የቡድን ውይይት ወቅት፣ የገጠራማው አዳ አፋ ነዋሪዎች እንደ ገለጹት በአንጻራዊነት ዝቅተኛ የብድር ምንጮች መታየታቸው ብድርን ለማግኘት ያሉት አማራጮች ጥቂት ብቻ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ ከዚህ በታች እንደተተነተነው፣ ከሁለቱ ማኅበረሰቦች ጋር ሲነጻጸር በአዳ አፋ ከሚገኙት ቤተሰቦች መካከል ማኅበረሰብ-ተኮር አማራጭ የብድር ምንጭ የሚያገኙት ጥቂቶች ናቸው፡፡

በሦስቱም ማኅበረሰቦች ዘንድ አማካይ የብድር ድግግሞሽ ብዛት እና አማካይ የምንጮች ቁጥር ተመሳሳይ መሆኑ፣ በብድር ምንጮች መካከል ያለው ልዩነት በበለጠ መጠናት እንደሚያስፈልገው ያመላክታል፡፡ መንግሥት ድጋፍ የሚያደርግላቸውና እንደ መግዛት እና መሸጥ ያሉ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን የሚያከናውኑ የሕብረት ሥራ ማኅበራት በአብዛኛው በብድር ምንጭነት በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ከሕብረት ሥራ ማኅበራት የሚገኘው ወጥነት እና ድግግሞሽ ያለው የብድር አገልግሎት መስጠታቸውም፣ እንደ አነስተኛ የብድር ተቋማት ያሉ ተቋማት ቅርንጫፎች በከተማዎች ውስጥ ብቻ ሲሆን፣ የማኅበራቱ መገኛ በማኅበረሰቦቹ መካከል ከመሆኑ የተነሣ ነው፡፡[3]

### 5.5. የአነስተኛ ብድር ተቋማት

መንግሥታዊ የሆኑ ምንጮች እንዳመላከቱት ከአነስተኛ የብድር ተቋማት የሚገኘው የብድር አገልግሎት ጥቂት መሆኑ፣ ስለ ተቋማቱ ጥቂት ማለት ያስፈልጋል (የግርጌ ማስታወሻ 3ን ይመልከቱ)፡፡ መንግሥት የአነስተኛ ብድር ተቋማትን ከማስተዳደር በተጨማሪ ድጎማ የሚደረግባቸው የግብርና ግብአቶችን በዱቤም ጭምር ያቀርባል፡፡ ማኅበረሰቦቹ ውስጥ ሥራቸውን የሚከውኑት የግብርና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች እነዚህን ሁለቱንም (ግብአቶች እና አነስተኛ ብድር) ያስተዋውቃሉ፡፡ ለግብርና የሚሆን ብድር 'ከአነስተኛ የብድር ተቋሙ' እንደሚገኝ ተደርጎ መታሰቡ አይቀርም፣ ምክንያቱም ሁለቱም በመንግሥት የሚተዳደሩ ሲሆኑ፣ የሚሰጡትን አገልግሎት የሚያስተዋውቁትም በእነዚሁ የመንግሥት ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አማካኝነት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ፣ የአነስተኛ ብድር ተቋማት የብድር አገልግሎት (ሀ) በአነስተኛ የብድር ተቋማት አማካኝነት የሚሰጥ የብድር አገልግሎት እና (ለ) በቀጠናው የግብርና ቢሮ የሚሰጥ የብድር አገልግሎት ጥምረት ተደርጎ በበዛ መጠን ተዋውቋል፡፡

ከአነስተኛ ብድር ተቋማት ብድር መውሰድ በአብዛኛው ማኅበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የሚያመላክተው ከዳሰሳው የተገኘ ቁጥር፣ ከመንግሥት የሚገኝ ብድር ከመንግሥት ምንጮች የሚገኝ የብድር አገልግሎትን ያለመፈለግን ነው፡፡ የማኅበረሰቡ

---

[3] ከወላይታ ዞን የገንዘብ እና ምጣኔ ሀብት ልማት ቢሮ የተገኘው መረጃ እንዳመላከተው (በሜይ 14፣ 2015 የዞን መስተዳድር ቢሮው ለዚህ ጥናት አጥኚዎች የተሰጠ)፣ ሦስቱ ማኅበረሰቦች ከሚገኙበት ቀጠና ውስጥ በ2013 ዓ.ም. 5% የሚሆኑት ብቻ ናቸው ከአነስተኛ ብድር ተቋማት ብድር ያገኙት፡፡

አባላት የዕዳ አከፋፈሉ አማራጭ የማይሰጥ ከመሆኑ የተነሣ ከአነስተኛ የብድር ተቋማት የሚሰጥ ብድር የመጨረሻ አማራጫቸው እንደ ሆነ ገልጸዋል፡፡ በመረጃ መሰብሰብ እና ጥናት ተኮር ቡድን ውይይቱ ወቅት ብዙ ግለሰቦች የአነስተኛ የብድር ተቋማት የዕዳ አከፋፈል አማራጭ ማሳጣት የተነሳ መከፋታቸውን ገልጸው፣ ዝናብ ባለመጣሉ ምክንያት እና ዕዳቸውን መክፈል ባለመቻላቸው በቀጣዩ አመት መሬታቸው የተወረሰባቸውን ቤተሰቦች ታሪክም ተናግረዋል፡፡ የሁለቱ ዋነኛ የብድር ምንጮች፣ የሕብረት ሥራ ማኅበራት እና አነስተኛ የብድር ተቋማት፣ ከፍተኛ የወለድ መጠን ስለሚያስከፍሉ፣ ገበሬዎች በብድር አገልግሎት ከሚገባው ያነሰ አገልግሎት እንደሚያገኙና ከመጠን በላይ እንደሚከፍሉ ያለውን ድምዳሜ ይደግፋል (ISF, 2013)፡፡ ሁሉም ዓይነት ብድሮች፣ በተለይም ዝቅተኛ የወለድ መጠን የሚያቀርቡቱ ለሁሉም የማኅበረሰብ አባላት በእኩል መጠን እንደማይቀርቡ የተገኘውን ድምዳሜ ያስታውሳል Guerin et al. (2013)፡፡

### 5.6. አካባቢያዊ አበዳሪዎች እና ማኅበረሰብ-ተኮር ብድር?

ከመኸር የሚገኘውን ገቢ በማሰብ ከመኸር ቀደም ብሎ ከነጋዴዎች መበደር ብዙም አልተለመደም፡፡ ለዚህም ምክንያት ተደርገው የተቀመጡት፣ ነጋዴዎች ማኅበረሰቡ ውስጥ የሚሰሩ አለመሆኑና ዕዳ እንዲከፈላቸው ለማድረግ የሚያስችል ምንም ዓይነት ሕጋዊ ዘዴ የሌላቸው መሆኑ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ፣ ብድር አብኛውን ጊዜ የሚካሄደው ከፍተኛ መተማመን ያላቸው ግለሰቦች ወይም ብድር የሚሰጡ ነጋዴዎች ጋር ግንኙነትን በሚጨምሩ ማኅበራዊ ትስስሮች መካከል መሆኑም ተጠቅሷል፡፡ እንደ ሕብረት ሥራ ማኅበራት ሁሉ፣ አናሳ የማኅበረሰቡ አባላት እና ግለሰቦች እንዲህ ያለውን የብድር አገልግሎት የማግኘት ዕድል ስለሌላቸው፣ ከመደበኛ የብድር ምንጮች ለመበደር ይገደዳሉ፡፡ በኢትዮጵያ መደበኛ ያልሆኑ ትስስሮች ሁኔታ ላይ ማኅበራዊ ትስስሮች አይነተኛ ገጽታ ያላቸው እንደ ሆን(Santos and Barrett, 2011) ወይም እንዳልሆን (Caudell et al., 2015) ለማየት የተደረጉ ጥናቶች የሚያሳዩት የተጣረሰ መረጃ ነው፡፡ እነዚህ ጥናቶች ያተኮሩት እንደ ሀብት እና የቤተሰብ መጠን ያሉ የቤተሰብ ባህሪዎች ሲሆን፣ በገጠሩ የኢትጵያ ዐውድ ሊጠቅሙ የሚችሉ እንደ ብሔር፣ ቋንቋ፣ ሓይማኖታዊ ትይይዝ እና የፖለቲካ ግንኙነት ያሉ ክፍፍሎችን አላሰሉም፡፡ በGuerin et al. (2013) እንደታየው የብድር አገልግሎት ተጠቃሚነት እና ዕዳ የሚታዩት ባለው ማህበራዊ-ባህላዊ እና ፖለቲካዊ አውድ ውስጥ መሆኑ፣ ለአንዳንዶች የተሻለ ዕድል ሰጥቶ ሌሎችን የማያካትት ይሆናል፡፡ በእነዚህ ሦስት ማኅበረሰቦች መካከል ገበሬዎች ብድር ለማግኘት እንዲችሉ ማኅበራዊ ትስስር ያላቸው መሆኑ ዓይነተኛ ሲሆን፣ መደበኛ ያልሆነ ብድር ተጠቃሚ ለመሆን የመቻል ሁኔታ በግላዊ ትስስሮች፣ ብሔር እና ሃይማኖታዊ ትስስሮች የሚገደብ ሲሆን፣ መደበኛ የሆነ የብድር አገልግሎት የማግኘት ሁኔታ ደግሞ በፖለቲካዊ ትስስር የሚወሰን ነው፡፡

የአዳ አሩ የአካባቢያዊ ብድር እና ሌሎች ማኅበረሰብ ተኮር የብድር ዘዴዎች ቤተሰቦች ከማኅበረሰብ ተኮር የብድር አካሄድ ይልቅ በአካቢያዊ አበዳሪዎች አገልግሎት ተጠቃሚዎች በመሆናቸው ከአዶሮና ቡጂ ይለያሉ፡፡ በድህነት ሁኔታ የማኅበረተሰቡን ደረጃ ከፋፍሎ የሚያሳይ አሰራር ባይገኝም፣ በአዳ አሩ የሚገኙ ቤተሰቦች በአማካይ ከሌሎቹ ሁለት ማኅበረሰቦች በባሰ የድህነት ሁኔታ እንደሚገኙ የሚያሳዩ ጠቋሚዎች ይገኛሉ፡- (1) በጥናቱ ውስጥ ከተካተቱት ሌሎች ማኅበረሰቦች ጋር ሲነጻጸር፣ በአዳ አሩ የሚገኙት ቤተሰቦች የባሰ የምግብ ዋስትና ማጣት ይታይባቸዋል፣ (2) ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ የሚያስችላቸውን ወጪ ለመሸፈን ያላቸው አቅም ዝቅተኛ ነው፣ እንዲሁም (3) ከፍተኛ የሆነ ያልተማረ ሰው ኃይል ስደት ይስተዋልባቸዋል (Cochrane and Vercillo, 2017)፡፡ ሌላኛው በሦስቱ ማኅበረሰቦች መካከል ያለውን አንጻራዊ ድህነት ጠቋሚ ደግሞ በ2005 የምግብ ዋስትና የሌላቸውን የገጠር ቤተሰቦች ለመደገፍ የተጀመረው የፕሮዳክቲቭ ሴፍቲኔት መርሃ-ግብር ተጠቃሚነት መጠን ነው፡፡ ከመርሀ ግብሩ በቅቶ መመረቅ እስከ 2011 ድረስ ያለመጀመሩ ዓመቱ በእነዚህ ሦስት ማኅበረሰቦች ዘንድ ያለውን ሁኔታ ለመመዘን እንደ ጠቋሚ ሊውል ይችላል፡፡

**ሰንጠረዥ 2. ብድር ለመውሰድ የተሰጡ ምክንያቶች ድግግሞሽ**

| ምክንያት | አዶሮ (%) | አዳ አሩ (%) | ቡጂ (%) | አጠቃላይ (%) |
|---|---|---|---|---|
| የግብርና ግብአቶች | 27 | 30 | 23 | 27 |
| መሠረታዊ ፍላጎት | 39 | 32 | 36 | 35 |
| የጤና ክብካቤ ወጪ | 23 | 22 | 36 | 25 |
| የቀብር ወጪ | 2 | 4 | 0 | 3 |
| የጋብቻ ወጪ | 2 | 2 | 2 | 2 |
| የትምሕርት ወጪ | 6 | 6 | 3 | 6 |
| ሌሎች | 0 | 5 | 0 | 2 |

የሴፍቲኔት መርሀ ግብሩ ድጋፍ ያደረገው በቡጂ 14% ብቻ (1,425 ቤቶችን ከ10,048 መካከል)፣ በአዴሮ 24% (1,207 ቤቶችን ከ5,047 መካከል) እና በአዳ አፋ 31% (1,184 ቤቶችን ከ3,784 መካከል) ነው፡፡[4] የሴፍቲ ኔት ተጠቃሚነት የሚወሰነው በቤተሰቦች የሀብት ደረጃ ልክ ሲሆን[5]፣ እስካሁን ሊገኝ የቻለው መረጃ የሚያመላክተው ሦስት እጅ የሚያህለው የአዳ አፋ ሕዝብ ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለበት ሲሆን፣ ይህም ከአጎራባቹ አዴሮ መንደር በሚስተዋል መልኩ ከፍተኛ ሲሆን፣ ከቡጂ ደግሞ በሁለት እጥፍ ይበልጣል፡፡

## 5.7. የብድር ምክንያቶች

የብድር ምክንያቶችን አስመልክቶ ከሦስቱ የወላይታ ማኅበረሰቦች የተገኘው መረጃ የብድር አካሄድን (ሰንጠረዥ 2ን ይመልከቱ) አካባቢያዊ ባህሪ የሚያመላክት ሲሆን፣ እጅግ ተደጋግሞ የተጠቀሰው ብድር የመውሰድ ምክንያት መሰረታዊ ፍላጎትን ማሟላት ነው (35%)፡፡ በቀጣይነት የተጠቀሰው ለግብርና የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ለመግዛት (27%) ሲሆን፣ ቀጣዩ ደግሞ የሕክምና አገልግት ለማግኘት ነው (25%)፡፡ ለግብርና የሚያስፈልጉ ግብአቶች ግዢ ቀዳሚ ተደርጎ ቢቆጠርም፣ የጤና አገልግሎትን እና ትምህርትን እንደ መሠረታዊ ፍላጎቶች አድርገን ከቆጠርን፣ ከአጠቃላዩ ከግማሽ የሚበልጡት (66%) የተወሰዱት መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት እንደ ሆነ ሊታሰብ ይችላል፡፡ እንደ ተሻሻለ ዘር እና ማዳበሪያ ያሉ የግብርና ግብአቶች ላይ ገንዘብ ማውጣት የተሻለ ገቢ የማስገኘት ዕድል ቢኖረውም፣ የመጨረሻው ውጤት ለመተንበይ በሚያስቸግረው የዝናብ መጣል ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል (Cochrane and Gecho, 2016)፡፡ ስለዚህ፣ እነዚህ ወጪዎች የተሻለ ገቢን እንደሚያስገኙ (የማስገኘት አቅም በእርግጥም አላቸው) የማስላት ጉዳይ ብቻ አይደለም፣ ምክንያቱም ከሌሎች ተጨማሪ ጉዳዮች የተነሳ የታሰበው ውጤት ላይ ላይደረስ ይችላል፡፡  ለዚህ ጥያቄ የሚሆነው መረጃ፣ ቤተሰቦች እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ እርግጠኛ ካለ መሆናቸው የተነሳ በአጠቃላዩ አካሄዶቹን የሚያመላክት እንደ ነበረ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ በመሠረታዊነት፣ ለተለያየ ፍላጎት ተብለው የተሰጡት እነዚህ ብድሮች ለአንድ ዓላማ ብቻ የሚውሉ እንዳልሆኑ ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ የተጠቀሱት ምክንያቶች በተሳታፊዎቹ አማካኝነት የተነሱትን ዓብይ ጉዳዮች ያሳዩ ቢሆንም፣ ሁሉንም ምኪያቶች አያጠቃልልም፡፡

ሕንድ ውስጥ የተካሄደ አንድ ጥናት (Guerin et al., 2013) እንዳመላከተው፣ አብዛኛው ብድር የሚወሰደው ልዩ ልዩ የሥራ ግብአቶችን ለመግዛት፣ ቤትን አሻሽሎ ለመገንባት ወይም የቁም ከብቶችን ብዛት ለመጨመር ሲሆን (30%)፣ የቤት ውስጥ ወጪዎችን ለመሸፈን (21%) በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ባህላዊ ስነስርዓቶችን እና በአላትን ለማካሄድ (17%)፣ ጤና ነክ ወጪዎች (13%) እና የትምህርት ወጪዎች (10%) በቀጣይነት ተቀምጠዋል፡፡ በእነዚህ ማኅበረሰቦች ዘንድ እነዚህ ምክንያቶች በተደጋጋሚ አልተጠቀሱም፡፡ አንዳንድ ትልልቅ ብድሮች የተወሰዱት እንደ ሞተር ሳይክል እና በአህያ የሚጎተቱ ጋሪዎች ያሉ ውድ መገልገያዎችን ለመግዛት (ሁለቱም እንደ 'ሌሎች ወጪዎች' የተካተቱ ናቸው) እንዲሁም ወጪ የበዛባቸው የሠርግ እና የቀብር ስነስርአቶችን ለማከናወን ቢሆንም፣ ለእነዚህ ጉዳዮች ብሎ ብድር የመውሰድ ሁኔታ በሌሎቹ ጥናቶች (እንደ Case et al., 2013; Guerin et al., 2013; Krishna, 2010 ባሉ) ከታየው ያነሰ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በጥናት ተኮሩ የቡድን ውይይት ወቅት፣ ለባህላዊ ስነ ስርዓቶች የሚወሰድ ብድር ትኩረት ተሰጥቶበት የነበር ቢሆንም፣ ትኩረቱ ግን ከብድሩ መጠን መብዛት እና ከዚያ የተነሳ የሚታወቁ ዕዳን ለመክፈል ያለመቻል ሁነቶች ስለ ተከሰቱ ነው፡፡ ተለይተው የሚታወቁ ግለሰቦች እና ቤተሰቦች ለሕይወት ዘመን ባለ ዕዳነት ለምሳሌ በቀብር ወይም ሠርግ የተነሳ መዳረጋቸው የታወቀ ቢሆንም፣ በዓይነታዊ መረጃ ብቻ ተመስርቶ ከሚታሰበው ያነሰ ሊሆን ይችላል፡፡ የቤት ለቤት የመጠይቅ ዳሰሳው  እንዳመለካተወው ለባህላዊ ስነ ስርዓቶች ብለው ብድር የሚወስዱ ቤቶች ብዛት አነስተኛ ነው፡፡ አብዛኞቹ ምላሾች እንዳሳዩት ብድር የሚወሰደው መሠረታዊ ፍላጎቶችን እና የጤና ክብካቤ አገልግሎትን ለማሟላት ሲባል ሲሆን፣ እነዚሁም በጥናት ተኮሩ የቡድን ውይይት ወቅት ገንዘብ የሚበደር "ሁሉም"፣ "እያንዳንዱ ቤተሰብ"፣ "ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ አብዛኛው"፣ እና "ማንም ከዕዳ ነጻ አይደለም" በሚሉት ሀረጎች አማካይነት ተጠቃልሏል፡፡ ሆኖም ካሁኑ ጊዜ ይቅ ባለፉት ጊዜያት ባህላዊ ግዴታዎችን ለመፈጸም ሲባል ከፍተኛ መጠን ያለው ብድር መውሰድ ዐብይ ምክንያት እንደነበረም ተጠቅሷል፡፡ ከእነዚህ አመላካቾች አንዱም በወላይታ ያለው አካባቢያዊ መንግስት ትልቅ መጠን ያላቸው እና አንዳንዴም ለሕይወት ዘመን የሚተርፉ ዕዳዎን ለማስቀረት እንዲህ ያሉ ብድሮች እንዳይከናወኑ ሕግ ማውጣቱ ይጠቀሳል፡፡ በአዳ አፋ ያለው አካባቢያዊ መንግስት በዓላትን በውድ ሁኔታ ለማከናወን ሲባል ትልቅ መጠን ያለውን ብድር የሚወስድን ሰው በእስር እንደሚቀጣ አሳስቧል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚከሰተው ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ አይደለም፣ በስዋዚላንድ እና ደቡብ አፍሪካ ቤተሰቦች የሚጠበቅባቸውን አይነት ሰፊ በዓል ለማከናወንና በማኅበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ስፍራ ለማጠበቅ ሲሉ በዕዳ መዘፈቃቸው ታይቷል (Case et al., 2013)፡፡

---

[4] የማኅበረሰብ የብዛት መጠንን የሚያሳየው መረጃ ከወላይታ ዞን መስተዳድር የተገኘ ሲሆን፣ የፕሮዳክቲቭ ሴፍቲ ኔት መርሀ ግብር ተጠቃሚነት መረጃው የተገኘው ደግሞ ከዳሞት ጊሌ የግብርና ቢሮ ነው፡፡

[5] መርሀ ግብሩ እንዲተገበር የታሰበው በዚሁ መንገድ ነው፡፡ በተግባር ግን ከዚህ የበለጠ ውስብስብ ነው፣ Cochrane and Tamiru, 2016ን ይመልከቱ፡፡

### 5.8. የግኝቶቹ ማጠቃለያ

ጥናቱ በተካሄደባቸው ሦስት ማኅበረሰቦ ውስጥ የታየው የአነስተኛ መሬት ባለቤት የሆኑ ገበሬዎች ልምድ እንዳመላከተው፣ ቤተሰቦች ገንዘብ የሚበደበት እና ባለ ዕዳ የሚሆኑበት ምክንያት ነጠላ ወይም በቀጥታ ተለይቶ ሊታይ የሚቻል እንዳልሆነ ነው፡፡ ብድር ለብዙ ምክንያቶች የሚወሰድ ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ ቤተሰቦች የሚበደሩት እንደ ምግብ፣ ትምህርት፣ እና የጤና ግልጋሎት ያሉ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ሲባል ነው፡፡ በእነዚህ ጊዜዎች፣ ብድር እና ባለ ዕዳነት ስለሚተሳሰሩ እና ስለሚመጋገቡ ተጠላልፈው ይታያሉ፡፡ በጠለቀ ድህነት ውስጥ የሚኖሩ አንዳንድ ቤተሰቦች በቂ ምግብ ቤት ውስጥ እንዳለ ለማረጋገጥ ሲሉ ከመበደር ሌላ አማራጭ የሌላቸው ሲሆን፣ ይህም ይብስ ወደ ከፋ ድህነት ይገትታቸዋል፡፡ ሌሎቹ ቤተሰቦች ደግሞ ለግብርና ግብአቶች በሚሆን ወጪ እና በመሳሰሉ ሌሎች ጉዳዮች የተነሳ ቢበደሩም፣ መኸር በመበላሸቱ፣ ወይም ደግሞ ዕዳን ለመክፈል ባለመቻል ለድህነት በከፋ ሁኔታ የሚጋለጡ ሲሆን፣ ወደ ንብረት መመናመን እና ዕድልን ወደ መቀነስ ያመራል፡፡ ገበሬዎች አስፈላጊውን ወጪ ለማድረግ እና ምርታቸውን ለማሻሻል የብድር እጥረት ያለባቸው ቢሆንም፣ ይህ የገንዘብ እውነታ የገጠር ባለ አነስተኛ መሬት ይዞታዎችን የኑሮ ዐውድ ከግምት ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡ የቁም ከብቶችን መግዛት የገንዘብ ጥቅም እንደሚያስገኝ ገበሬዎች ቢስማሙም፣ የአብዛኛዎቹ ችግር ግን መሠረታዊ ምግብ፣ የጤና ክብካቤ እና ትምህርት ማሟላት መቻል ነው፡፡ ምርቱ ሊተነበይ በማይችል የዝናብ ሁኔታ ላይ ጥገኛ ሆኖ ሳለ ንብረት እና መሬታቸውን ከብቶች በመግዛት ለማጣት አይፈልጉም፡፡ ለአብላጫዎቹ (መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚበደሩት 66%)፣ እንደዚህ ያው ወጪ ቤተሰቡ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት እዳ እየገባ ባለበት ሁኔታ ውስጥ የማይታሰቡ ሲሆኑ፣ እነዚያን ትንንሽ መጠን ያላቸው ብድሮች ለመክፈል ያልቻሉበት ሁኔታ በተደጋጋሚ ገጥሟቸዋል፡፡

## 6. ማጠቃለያ

ይህ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ባላቸው ገበሬዎች እና ዕዳ መካከል ባለው ግንኙነት ላይ የተሠራ መጠናዊ እና ዓይነታዊ ምዘና እንዳመላከተው፣ 'የቁጠባ ባህል'ን ማበረታታት እና ማስተዋወቅ ቁጠባ እንዳይካሄድ ከሚገድቡ ጉዳዮች አንጻር ሊታሰብ ይገባል፡፡ ከአስርት ዓመታት በፊት እንደ ታየው (Ferguson, 1994) እንዲህ ያለው ቅስቀሳ ለአንድ ስፍራ እና ወቅት የሚጠቅመውን የቁጠባ ዓይነት ከግምት ማስገባት አለበት፡፡ በተጨማሪም፣ በግለሰቦች እውቀት እና የባህሪ ለውጥ ላይ የሚያተኩሩ ፖሊሲዎች እና መርሀ ግብሮች፣ ስርዓታዊ ገደቦችን፣ በተለይም አነስተኛ ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች በዕዳ የተዘፈቁበትን መጠን ግምት ያስገባ ሰፊ ምዘና ማካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የብድር መጠን፣ ድግግሞሽ፣ እንዲሁም ምንጮች እና ዕዳ  አነስተኛ የመሬት ይዞታ ባላቸው ገበሬዎች ዘንድ የሚያስከትሉትን ያልተጠና ከቁጠባ ወይም ከንብረት ማፍራት መገደብ ዳሰስናል፡፡ ግኝቶቹም ዕዳ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ባላቸው ገበሬዎች ዘንድ ያለውን ውስብስብ እና አካባቢዊ ዐውድ እንዲሁም ገፍቶ የሚያልፍ ተፈጥሮውን ያመላክታል፡፡ አንዳንድ የጥናት ጽሑፎች እንዳሳዩት በአንጻራዊነት ባለጸጋ የሆኑት በበለጠ ሁኔታ ይበደራሉ (Nuansoi, 2013)፡፡ የዚህ ጥናት ግኝቶች እንዳሚያመላክቱት ለችግር ተጋላጭ ከመሆን የተነሳ ለብድር የሚጋለጡ ሲሆን፣ ብድር የሚከናወነው እንደ መጨረሻው አማራጭ ሆኖ ነው፡፡ ከጥናቱ ግኝቶች አንዱ በኢትዮጵያ ዐውድ ውስጥ አነስተኛ የብድር ተቋማት በመንግሥት የሚተዳደሩና ዕዳን የመክፈያ አማራጭ የማይሰጡ ከመሆናቸው የተነሳ ቤተሰቦች ዕዳቸውን ለመክፈል ካልቻሉ የከፋ ሁኔታ (መሬትን ማጣት) የሚከሰት መሆኑ ነው፡፡ ለመክፈል ያመቻላቸውም በአብዛኛው ሊገመት ከማይቻል የዝናብ ሁኔታ እና ከመሳሰሉ ውጫዊ መንስኤዎች የተነሳ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ፣ በተጨማሪም ያልተሟላ የብድር ፍላጎት ቢኖርም በመላው የገጠር አካባቢ ለምን የአነስተኛ ተቋማት የብድር አገልግሎት ዝቅተኛ እንደ ሆነ ያሳያል፡፡ ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ በሚገባ ያላደገ ቢሆንም፣ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች የተሻሻለ ዘር እና ማዳበሪያ ለመግዛት ወጪ ማውጣትን የመሳሰሉ መልካም አጋጣሚዎችን ተጠቃሚ ሆነው፣ ከወጪዎቻቸው ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ የተጋላጭነት ሁኔታዎችን፣ እንዲሁም አጠቃላይ መኸራቸውን፣ በዚያውም ገቢያቸውን ከእነርሱ አቅም ውጪ በሆነ መንገድ ከማጣት የሚከላከሉበት የኢንሹራንስ አቅም ሊኖራቸው ይችል እንደ ሆነ ሊጠና ያስፈልጋል፡፡

በሌሎች የጥናት ጽሑፎች ውስጥ (Case et al., 2013; Guerin et al., 2013) የብድር ምክንያቶች ተለያይተው የተቀመጡ ሲሆን፣ የዚህ ጥናት ግኝትም አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች የብድር ምክንያት ልዩ ልዩ እንደ ሆነና፣ ጥቂት ለማኅበራዊ-ባህላዊ በዓላት አከባበር ሲባል የሚወሰዱ ብድሮች እንዳሉ ያሳያል፡፡ ግኝቶቻችንን በስፋት ከሌሎች  የጥናት ጽሑፎች ጋር ስናስተያይ፣ ልንደርስባቸው የቻልናቸው አራት ዋና ዋና ድምዳሜዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1) መበደር፣ ማበደር እና ዕዳ ባለው ማኅበራዊ-ባህላዊ መቼት ውስጥ የሚከናወኑ አካባቢያዊ ሂደቶች ሲሆኑ፣ የትኛው የማኅበረሰብ ክፍል የገንዘብ አቅርቦት አገልግሎት እንደሚያገኝ እና በምን አይነት መንገድ እዳ እንደሚከፈል ይወስናል፣
2) በገጠር ልማት ውስጥ ዕዳ የሚጫወተው ሚና ላይ የተሻሻለ ግንዛቤ መገኘቱ ፖሊሲዎች እና መርኃ ግብሮች እንዲያው በመላ ምት ከመከናወን ይልቅ፣ ወይም ዕዳ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚጫወተውን ሚና ቸል ከማለት ይልቅ፣ ጋሬጣዎችን ነጥሎ ለማውጣትና እነርሱን ለማስወገድ ይረዳል፣
3) አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸውን ገበሬዎች ለማገዝ የሚቀረጹ ፖሊሲዎችና መርሀግብሮች ለባለዕዳነት ምክንያት የሚሆኑትን መንስኤዎች  በተሻለና ሰፊ ስርዓታዊ ምዘና ውስጥ በማካተት ትግበራዎቻቸውን ከነርሱ አንጻር ሊያከናውኑ ያስፈልጋል፣

4) አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች በድህነት እንደተዘፈቁ የሚቀሩት እና በቀጣይ የምግብ ዋስትና ማጣት የመቸገራቸው ዋነኛ ምክንያት ዓመታዊ እና ለረዥም ጊዜ የዘለቀ ዕዳ ነው፡፡

ለገጠር ገበሬዎች መደበኛ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማሻሻል እና ለማስፋፋት ብዙ ትኩረት የተሰጠ ቢሆንም፣ ገበረዎች ለቁጠባ የሚመርጧቸው መንገዶች ቸል ተብለዋል፡፡ በዚህ ስራ ውስጥ የተጠቀሱ በዓለም-አቀፍ አካላት፣ መንግሥታት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እና ተማራማሪዎች የተሠሩ ምርምሮች ቁጠባ በፋይናንስ ጉዳዮች ላይ ብቻ የተገደበ ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ ይህ ጥናት ያተኮረው በገንዘብ ብድር እና ዕዳ ላይ ነው፡፡ ሆኖም፣ ቁጠባ አያሌ ገጽታዎች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ ጋራ ኃላፊነት ከፍተኛ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ ማኅበራዊ ባህላዊ ግዴታዎች ከገንዘብ ቁጠባ ወደ ኋላ ሊያስቀሩ ይችላሉ፣ ምንያቱም እነዚህ የገንዘብ ቁጠባዎች የጋራ ኃላፊነቱን በሚጋሩ ሁሉ በቀላሉ በጥቅም ላይ ሊውሉ ወይም ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡ በእነዚህ ዐውዶች ውስጥ 'ቁጠባ' እንደ ቁም ከብት ባሉ ለረዥም ጊዜ የሚቆዩና በቀላሉ ወደ ገንዘብ የማይለወጡ ንብረቶች አማካኝነት ቢሆን የተመረጠ ነው (Ferguson, 1994)፡፡ አብዛኛው ብድር መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት በሚወሰድበት እንደ ኢትዮጵያ ባለ ሁኔታ ከገንዘብ ይልቅ እንደ ከብቶች ባለ ንብረት መልክ መቆጠብ የተሻለ መነሳሳትን ይፈጥራል፡፡ የቁጠባን አካሄድ እና ቀዳሚነት ያላቸው ክንውኖች በተሻለ ለመረዳት ወደ ፊት ተጨማሪ ስነ-ሰብዕ እና መጠናዊ ጥናቶች ሊካሄዱ ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት በወላይታ የሚኖሩ ቤተሰቦች ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን እና ድንገተኛ ክስተቶችን የመቋቋም አቅማቸውን ለማዳበር በልጆቻቸው ትምህርት ላይ ወጪን ማውጣት፣ የሚዘሯቸውን ዘሮች እንደ የፍራፍሬ ዛፎች የመሳሰሉትን ጨምሮ በማብዛት፣(Cochrane and Gecho, 2016) በቀጥታ ከገንዘብ ጋር ያልተያያዙ ማሻሻያዎች ላይ ወጪ ያወጣሉ፡፡ በተለይም በገንዘብ መልክ የሚከማች የንብረት ማፍራት ከቁጠባ አንጻር እንዴት እንደሚታይ ለመረዳት ተጨማሪ ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ጥናት በተካተቱት ማኅበረሰቦች መካከል ገበሬዎቹ ቤተሰቦቻቸው ዕዳን በተደጋጋሚ ለመክፈል ከሚቸገሩበት እና ለመቆጠብ ከማይችሉበት ሁኔታ ሳይወጡ፣ ማኅበረሰቡ የሚያስተዳድራቸው የቁጠባ ቡድኖች እንዲሁም ሌሎች መርሀግብሮች አማካኝነት የቁጠባ ባህልን የሚያስተዋውቁ አካላት የሚኖራቸው ተጽዕኖ አነስተኛ እንደ ሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በማኅበረሰቦቹ መካከል የሚታየው ብድር እና ባለዕዳነት ልዩነት አናሳ መሆኑ የሚያሳየው፣ Rahmato (2007) እንዳብራራው በወላይታ ዞን የሚገኙ ቤተሰቦች የመሬት ይዞታ መጠን የየቤተሰባቸውን መሠረታዊ ፍላጎት ለማሟላት ከሚያስችል ያነሰ መሆኑ ያስከተለባቸውን ዘላቂ ድህነት ነው፡፡ ቤተሰቦች ለጤና ክብካቤ አገልግሎት እድል የማያገኙ ወይም በቂ የሴፍቲ ኔት አማራጭ በአብዛኛው የማያገኙ መሆኑ፣ መሠረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት ንብረትን ለመሸጥና ለመበደር የሚያስገድዳቸው መሆኑ ድህነቱ ተቋማዊ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ከዚህም የተነሳ ቤተሰቦቹ በዓመታዊ ብድር ላይ እንዲደገፉ የሚያደርጋቸው ሲሆን፣ በከፊል ቋሚ የባለ ዕዳነት ሕይወት ውስጥ እየኖሩ፣ ጥቂት ኑሮን የሚያናጋ ሁኔታ ሲገጥማቸው ለማለፍ እንዲችሉ መበደር ይኖርባቸዋል፡፡ የዕዳ ተስፋፊነት እና ድግግሞሽ፣ የየእለት የብድር ምክንያቶች፣ ከፍተኛ ወጪ ከሚያስከትሉ የበዓል ወጪዎች በተቃራኒ፣ የከፍተኛ ወለድ መጠን ጫና፣ ዕዳን ለመክፈል የሚገጥሙ ፈታኝ ሁኔታዎች፣ እንዲሁም ዕዳን መልሶ ለመክፈል የሚደረግ ከፍተኛ ተስፋ፣ በድምሩ ሁሉም በድህነት መዘፈቅን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ በተጨማሪም፣ ቤተሰቦች ንብረታቸውን ወደሚያሳጣ እና ለበለጠ ተጋላጭነት ወደሚዳርጋቸው የተበዳሪነት ልማድ ሳይሄዱ የኑሮ መናጋትን እንዲቋቋሙ የሚያስችላቸው የአሰራር ለውጥ ካልተጨመረበት የባህሪ ለውጥን ማስተዋወቁ ያለው ተጽዕኖ የተገደበ ይሆናል፡፡

**ማጣቀሻዎች**


Ainsworth, M., Over, A.M., 1997. Confronting AIDS: Public Priorities in a Global Epidemic. World Bank, Washington.

Ali, D.A., Deininger, K., 2014. Causes and implications of credit rationing in rural Ethiopia: the importance of zonal variation. J. Afr. Econ. 23 (4), 493e527.

Amha, W., 2011. Meeting the financial needs of smallholder farmers in Ethiopia. In: Djurfeldt, G., Aryeetey, E., Isinika, A. (Eds.), African Smallholders: Food Crops,

Markets and Policy. CAB International, Cambridge, pp. 156e188.

Aredo, D., 1993. The Informal and Semi-formal Financial Sectors in Ethiopia: a Study of the Iqqub, Iddir, and Savings and Credit Co-operatives. Research Paper 21.

African Economic Research Consortium, Nairobi.

Bacon, C., Sundstrom, W., Gomez, M., Mendez, V., Santos, R., Goldoftas, B.,

Dougherty, I., 2014. Explaining the ‘hungry farmer paradox’: smallholders and fair trade cooperatives navigate seasonality and change in Nicaragua's corn and coffee markets. Glob. Environ. Change 25, 133e149.

Bloch, F., Rao, V., Desai, S., 2004. Wedding celebrations as conspicuous consumption: signaling social status in rural India. J. Hum. Resour. 39 (3), 675e695.

Case, A., Garrib, A., Menendez, A., Olgiati, A., 2013. Paying the piper: the high cost of funerals in South Africa. Econ. Dev. Cult. Change 62, 1e20.

Caudell, M., Rotolo, T., Grima, M., 2015. Informal lending networking in rural Ethiopia. Soc. Netw. 40, 34e42.

Chambers, R., 1995. Poverty and livelihoods: whose reality counts? Environ. Urban. 7, 173e204.

Chemonics International, 2006. Sustainable SACCO Development: Training Material (Report prepared for USAID).

Chiche, Y., Kelemu, K., 2012. Qualitative Gender Analysis in Gumuz, Shinasha and Berta Cultural Communities, Beninshagul Gumuz Region (Beninshangul Gumuz Food Security and Economic Growth Project report for Oxfam Canada).

CIA, 2015. Ethiopia. www.cia.gov/library/publications/the-world-factbook/geos/et.html.

Cochrane, L., Gecho, Y., 2016. The dynamics of vulnerability and adaptive capacity in southern Ethiopia. In: Companion, M., Chaiken, M. (Eds.), Responses to Disasters and Climate Change: Understanding Vulnerability and Fostering Resilience.

CRC Press, Boca Raton.

Cochrane, L., Tamiru, Y., 2016. Ethiopia's productive safety net program: politics, power and practice. J. Int. Dev. 28 (5), 649e665.

Cochrane, L., Thornton, A., 2016. Charity rankings: delivering development or dehumanising aid? J. Int. Dev. 28, 57e73.

Cochrane, L., Vercillo, S., 2017. Youth perspectives on migration, poverty and the precarious future of farming in rural Ethiopia. In: Bonifacio, G. (Ed.), Gender and Youth Migration: a Global Survey (Manuscript submitted for publication).

CSA, 2007. Population and Housing Census of Ethiopia. Central Statistical Agency, Addis Ababa.

Cull, R., Demirguc-Kunt, A., Morduch, J. (Eds.), 2013. Banking the World: Empirical Foundations of Financial Inclusion. MIT Press, Cambridge.

Deribie, E., Nigussie, G., Mitiku, F., 2013. Filling the breach: microfinance. Bus. Econ. Manag. 1, 10e17.

Estenson, P.S., 1987. Farm debt and financial instability. J. Econ. Issues 21 (2), 617e627.



Ferguson, J., 1994. The Anti-politics Machine: “Development,” Depoliticization and Bureaucratic Power in Lesotho. Cambridge University Press, Cambridge.

Fridell, G., 2013. Introduction e politicising debt and development: activist voices on social justice in the new millennium. Third World Q. 34 (8), 1492e1496.

Gecho, Y., 2014. Livelihood Strategies and Food Security of Rural Households in Wolaita Zone (Southern Ethiopia. Doctoral dissertation submitted to Haramaya University).

GoE (Government of Ethiopia), 2010. Growth and Transformation Plan. Ministry of Finance and Economic Development, Federal Democratic Republic of Ethiopia, Addis Ababa.

Gray, L., Dowd-Uribe, B., 2013. A political ecology of socio-economic differentiation: debt, inputs and liberalization reforms in southwestern Burkina Faso. J. Peasant Stud. 40 (4), 683e702.

Guerin, I., D'Espallier, B., Venkatasubramanian, G., 2013. Debt in rural south India: fragmentation, social regulation and discrimination. J. Dev. Stud. 49 (9), 1155e1171.

Handino, M.L., 2014. 'Green Famine' in Ethiopia: Understanding the Causes of Increasing Vulnerability to Food Insecurity and Policy Responses in the Southern Ethiopian Highlands (Doctoral dissertation submitted to the University of Sussex).

Holden, S., Bezu, S., Tilahun, M., 2016. How Pro-poor Are Land Rental Markets in Ethiopia? Norwegian University of Life Sciences (Centre for Land Tenure Studies Report).

ISF (Initiative for Smallholder Finance), 2013. Local bank financing for smallholder farmers: a $9 billion drop in the ocean. Briefing 01, 24 October 2013.

Krishna, A., 2010. One Illness Away: Why People Become Poor and How They Escape Poverty. Oxford University Press, New York.

McCann, J.C., 1995. People of the Plow: an Agricultural History of Ethiopia, 1800e1990. University of Wisconsin Press, Madison.

McMichael, P., 2013. Value-chain agriculture and debt relations: contradictory outcomes. Third World Q. 34 (4), 671e690.

Mohanty, B.B., 2005. 'We are like the living dead': farmer suicides in maharashta, western India. J. Peasant Stud. 32 (2), 243e276.

Nuansoi, W., 2013. The study on farmers' debt, loan repayment and guielines for debt settlement in the south of Thailand. Int. J. Agric. Food Sci. Technol. 4 (8), 835e840.

Rahmato, D., 1992. The Dynamics of Rural Poverty: Case Studies from a District in Southern Ethiopia. Monograph 2/92. CODESRIA, Dakar.

Rahmato, D., 2007. Development Interventions in Wollaita, 1960se2000s: a Critical Review. Forum for Social Studies, Monograph No. 4: Addis Ababa.

Salami, A., Kamara, A., Brixiova, Z., 2010. Smallholder Agriculture in East Africa: Trends, Constraints and Opportunities. Working Paper 105. African Development Bank Group, Tunis.

Sana, M. Stecklov, G., Weinreb, A. 2012. Local or outsider interviewer? an experimental evaluation. In: Submitted to the Annual Meeting of the Population Association of America, San Francisco, 3e5 May 2012.

Santos, P., Barrett, C., 2011. Persistent poverty and informal credit. J. Dev. Econ. 96, 337e347.

Scott, J.C., 1985. Weapons of the Weak: Everyday Forms of Peasant Resistance. Yale University Press, New Haven.

Soederberg, S., 2013. The politics of debt and development in the new millennium: an introduction. Third World Q. 34 (4), 535e546.

Steel, W., Aryeetey, E., Hettige, H., Nissanke, M., 1997. Informal financial markets under liberalization in four african countries. World Dev. 25 (5), 817e830.

Stover, J., Bollinger, L., 1999. The Economic Impacts of AIDS. Future Group International, Washington.

Tesfamariam, K., 2012. Determinants of saving behaviour of cooperative members survey evidence from Tigrai region, Ethiopia. J. Res. Econ. Int. Financ. 1,150e158.

Thornton, A., Kerslake, M.T., Binns, T., 2010. Alienation and obligation: religion and social change in Samoa. Asia Pac. Viewp. 51, 1e16.

Wilson, B., 2010. Indebted to fair trade? Coffee and crisis in Nicaragua. Geoforum 41,84e92.

World Bank, 2013. Ethiopia Economic Update II: Laying the Foundation for Achieving Middle Income Status. World Bank, Washington.